# ምእራፍ 11

## ወደ በጌምድር ጉዞ

ከዚህ በኋላ ሸህ ዘካርያስ ወደ በየምድር በተሻገሩ ጊዜ በክፉው ቀን ምክንያት ዋግና ላስታ የተሻለ ስለነበር ተከዜን እየተሻገረ በድህና በቋንባ በዋግና በላስታ ተሻግሮ ይኖር የነበረው ሕዝብ እሳቸውን ተከትሎ ወደ የነበረበት ተመለሰና ከነገላ እስከበለሳ እየተሻገረ ሰፈረ ። ሸህ ዘካርያስም ልጭ ተቀምጠው ማስተማር በጀመሩ ጊዜ በበጌምድር የነበረው እስላም ሁሉ በክርክር እንደማይቻለው ስለተገነዘበ ዘካርያስን በዝች ሰይፍ አንገቱን ቆርጬ ከዚያ ወዲያ የሆነ ይሁን በማለት ባለሰይፍ ስለት ሲያቀርብ ባለ ጠብመንጃው እንዲት ጥይት ለዘካርያስ አላጣም ይል ነበር ።

ሸህ ዘካርያስ ሐዋሪያዊ ጉዞ ለማድረግና በጊዜው ተሹመው ያስተዳድሩት ለነበሩት ለራስ ወልዴ ወደ ሊቦ ሄደው ስለተግባራቸው ማስረዳት እንደነበረባቸው ለተከታዮቻቸው እንዲዘጋጁ ካስጠነቀቁ በኋላ ሙሉ ዝግጅት ተደርጎ ጉዞው ተጀመረ ። ሸህ ዘካርያስ ከቤታቸው ሲወጡ ከተማሪው ጋር ሲቆጠር ከሶስት መቶ ያላነሰ ሰው ይከተላቸው ነበር ። የተቻለውን ያህል ስንቅ ለመያዝ ቢሞከርም ከክፉው ቀን ውጭ ስለነበር ጉዞው ታላቅ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ነበር ። ከቤታቸው ወጥተው ቆላ ቆላውን አቋርጠው ወደ በለሳ ተጉዘው ቡርሳ ከተባለው መንደር ከእሸቴ ውስይን ቤት ገቡ ። በግብርና የሚተዳደሩት አቶ እሸቴ ውስይን አስቀድመው ተዘጋጅተው ኑሮ ለሸህ ዘካርያስንና ተከታዮቻቸውን ሰንጋቸውን አርደው አስፈላጊውን ድግስ ደግሰው በመቆየታቸው እንኳን ለሰወቹ ለከብቶቹም የሽንብራ ገብስ ጎፈራ ፈሰሳቸው። ምንም የጎደለ የለለ መሰለውና ሁሉ ከመጠን ባለፈ ደስታ ተሞላ ። ሸህ ዘካርያስ ግን ጸጥ ብለው የሰውን ሁሉ ሁናቴ ሲመለከቱ እንግዳ ተቀባይ እሸቴ ወሰይን ቀረብ ብለው እስዎ እኮ ካቅማችን በላይ አጥብቀው ትልቅ



ስለሆኑብን ደፍረን ለመነጋገር አንችልም ዳሩ ግን እርስዎ ሲያነጋግሩን በጣም እንደሰታለን ስለዚህ ለሰሩት ሁሉ እርስዎን እርስዎ ይጠብቁታል እንጅ ለማንም ጉዳይ ለመምክር የሚችል ሰው የለም አሉና ተናገሩ ።

ሸህ ዘካርያስም ምላሽ ሲሰጡ እሸቴ ለለምክርህ ደስ ይለኛል እኔም አንተን ልመክርህ እወዳለሁ ይህን አገር አሁኑኑ ልቀቀው እባክህ የሚበጅህ አገር አይደለም ። እሸቴ ውሰይንም የኔታ ይህን የመሰለ መሬት ለቅቄ የት ልሄድ? አሉ ሸህ ዘከርያስም ወይራና ክትክታ አበቀል ወደሆኑ አገር ሄደህ ስፈር አሉና ይህን የመሰለ መሬት የምትለውን ያገኘኸው ጌታውን ገሎ ነው አንተም ከዚህ መቀመጥ ብትፈልግ ህይወትህን ለማጥፋት ቆርጠህ እንደምትቀመጥ እወቀው አሏቸው ። ሸህ ውሴንም በነገሩ እስብበታለሁ ብለው መለሱና እንግዶቻቸውን ሸኝተው ቃለ እግዚአብሔር ለመስማት ተዘጋጁ ። ወዲያው ተበልቶ ተጠጥቶ ሲያበቃ ሕዝቡ ተሰብስቦ ስብከት ሲጀምሩ ስለሃይማኖታችን ጉዳይ እስካሁን የምንመራበት መጽሐፍ ቁርአን ነው በሰው ቋንቋ ስለተጻፈ ሚስጥሩ ባይገባን ነው እንጅ የሙሴ ኦሪት የዳዋት መዝሙር የነበያት መጽሐፍትና የወንጌል ቃል ከሚያስተምሩን የተሰየ አይደለም ስለዚህ በወንጌል ቃል ማመን ትክክለኛ መሆኑን የኛው ቁርአን ሲናገር የኦሪትና የነበያት መጽሐፍት እንዲሁም የወንጌል አረጋጋጭ ነኝ በምንም አልለይም ይላል ። በቁርአን ገጽ 78 ምእራፍ 5 አል ሚእዳህ ክፍል ስድስት አንቀጽ 66- 68 ተመልከቱ ። እንዲሁም በቁርአን ገጽ 9 ምእራፍ 2 ክፍል 1 አንቀጽ 87 - 91 ያስረዳል ። በቁርአን ገጽ 10 ምእራፍ ሁለት ክፍል አራት እል በቅራህ ክፍል 1 አንቀጽ 93 በኦሪት ህግ እንዲሰሩ ያዛል ። ሙሴ ይሳ ነበያት ሁሉ በሰጡት የማንለይ ነን ብለን እናምናለን ። በቁርአን ገጽ 14 ምእራፍ ሁለት አል በቅራህ ክፍል 1 አንቀጽ 136 ተመልከት ።

በቁርአን ቃል በሙሴ ኦሪት በዳዋት መዝሙር በነቢያትና በወንጌል በጠቅላላ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን እንድንሰራባቸው ካዘዘን የሙሴ ኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 3 ቁጥር 15 እንዲህ ይላል ባንችና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ በዘርሽና በዘሯ መካከል እራሱ እራስሽን ይቀጠቅጣል አንችም ሽኮናውን ትቀጠቅጫለሽ ። ያለው የሴቲቱ ዘር ከማርያም የተወለደው የሱስ የባቡን የሰይጣንን እራስ ቀጠቀጠው ። ሰይጣንም የየሱስን እጅና እግር በሚስማር አስቸነከረው።

በመዝሙር 2 ቁጥር 11 ና 12 ለእግዚአብሔር በፍራት ተገዙ በርአድ ደስ ይበላችሁ ልጁን ስሙት እንዳይቆጣ ባላችሁበት መንገድ እንዳትጠፉ ቁጣው ጥቂት ቆይታ ትነዳለችና በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው ።

እንዲሁም ኢሳያስ ምእራፍ 9 ቁጥር 6 ህጻን ተወልዷልና ወንድ ልጅም ተሰጠነ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ። ስሙ ድንቅ ተብሎ ይጠራል መካር ብርቱም አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ። ኢሳያስ 53 ቁጥር 1-32 ስለሀጥያታችን መሞቱን ያስተምረናል በእርሱ ቁስል እኛ መዳናችን ይገልጽልናል ።

ዳንኤልም በበኩሉ በምእራፍ 9 ቁጥር 24ና 25 የቅዱሳን ቅዱስ መሲህና ንጉሥ ክርስቶስ ብሎ በሰሙ ይጠራዋል ።

ኦሪትና መዝሙር ነቢያትም ከዚህ በላይ እንደገለጸው ሲያስረዱ ወንጌልም በበኩሉ በሚከተለው ያስረዳል ።



ዮሐንስ ምእራፍ 3 ቁጥር 16 እግዚያብሔር እንዲሁ ዓለምን ወዱዋልና አንድ ልጁን እስኪለውጥ ድረስ በእርሱ ያምነ ሁሉ እንዳይጠፋ የዘላለም ህይወት ትሆንለት ዘንድ እንጅ ።

ማርቆስ ምእራፍ 16 ቁጥር 16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል ።

ማርቆስ ምአራፍ 28 ቁጥር 19ና 20 እንግዲህ ሂዱና አህዛቡን ሁሉ አስተምሩ አጥምቋቸውም በአብና በልጅ በመንፈስ ቅዱስ ስም ። በእርሱም ያዘዝኳችሁን ሁሉ መጠበቅ አስተምሯቸው እኔም እነሆ ከላንት ጋራ ነኝ በዘመን ሁሉ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ አሜን ።

የሚለውን ቃል በአረብኛ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ እና ቁርአን እያመዛዘኑ ካስረዱ በኋላ ሽህ ዘካርያስ ሰለራሳቸው ሲናገሩ እኔም እንደተላከሁት ቁርአኑ እራሱ በሚመሰክርላቸው መጽሐፍት አንደኛ ኦሪት ሁለተኛ መዝሙራት ሶስተኛ ነበያት አራተኛ ወንጌል በመልእክቱ የመሰከረለቱ የሱስ ክርስቶስን አምላክነቱንና መድሃኒትነቱን ተቀብሎ እንደትእዛዝ አምኖ መጠመቅ ተገቢ ነው ብለው ንግግራቸውን ደመደሙና ቁጭ ሲሉ እሽቴ ውሴን ጌታ አንድ ጥያቄ ልጠይቅ ይፍቀዱልኝ አሉ ሽህ ዘካርያስም በደስታ ጥያቄውን እቀበላለሁ ስላሉ እንዲህ በጥብቅ ማመንና መጠመቅ ለጽድቅ ተፈላጊ ከሆነ እርስዎ አሁንም አልተጠመቁ እራስዎ ተጠምቀው ምሳሌ ቢሆኑ ሕዝቡ በተሎ ክርስትናን እየተቀበለ የሚጠመቅ አይመስለወትም ወይ? አሉ ሽህ ዘካርያስም ሲመልሱ እኔ ከመጠመቅ የዘገየሁት ከተጠመቅሁ ማንም እስላም አያስገባኝም ምስክርነቴን ከሰጠሁ በኋላ ግን ጥምቀትን መቀበሌ የማይቀር ነው ሁሉም በጊዜው ይፈጸማል

ብለው መለሱላቸው ። እሸቴ ውሴንም ተምኖርበት ቦታ በእድሜ የማያኮራ ነው ። እርስወም ገልጸውልኛል እንግዲህ ከሁሉም ቅድምያ የምስጠው አስፈላጊውን ዝግጅት እድርጌ መጠመቅ ነው አሉና እንግዶቻቸውን ሸኝተው አስፈላጊውን ዝግጅት ከፈጸሙ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው እስከነቤተሰባቸው ተጠምቁ ። ክርስቲያን ሁነው ብዙ ሳይቆዩ ወዲያው ጥረግ የሆነ በሽታ ከቤታቸው ገባና እሳቸውና ልጆቻቸው ታመው ሶስት ቀን ያክል ቆዩና እሸቴ ውሴን ሞቱ ባለቤታቸው ወይዘሮ ጥሩ እሳቸውን ቀብረው ሲመለሱ ሴት ልጃቸው ሙታ ቆየች አሁንም እንደገና እርሷን ቀብረው ብዙ ሳይቆዩ ሁለት ወንዶች ልጆቻቸው ሞቱ ያሁሉ ደስታ የታየበት ቤት አራት አሬሳ ወጣበትና ወና ቀረ ። አልቃሽ ሲያስለቅስ እንዲህ አለ ይባላል ፤

ወሸኔ ደግነት ላምላክ መመቸት ፤
ትጸድቃለህ ቢሉት ተጠመቀ ፊት ፤
ሁሉን የሚረሳ ስለሃይማኖት ፤
የአምላክ መልክተኛ ሲመጣ ከቤት ፤
የተቀበላቸው በፈገግታ ፊት ፤
እሸቴ ውሴን የለውም ጉድለት ።

ከዚህ በላይ የዘረዘርኩላችሁን ጉዳይ የሰማሁት ከወላጅ እናቴ ነው ። ምክንያቱም በዚህ አኳኋን የሞቱባቸው አባታቸውና እህታቸው ሁለት ወንድሞቻቸው ነበሩ ። ሽህ ዘካርያስ ከቤታቸው ወተው በሚሰብኩበት ጊዜ አባቴም እናቴም ከዛው ያይን ምስክር ሁነው እይተው ሰምተዋል ። በህይወት በነበሩበት ጊዜ ለቤተሰባቸው ሲነግሩን የቆዩትን ስረሳ መልሽ መላልሽ እጠይቃለሁ እነሱ ግን በአይናቸው እያዩ የተፈጸመ ታምር ስለሆነ በፍጹም አይረሱትም ። ከዚህ ላቁምና የተነሳሁበትን የሸህ ዘካርያስን ጉዞ ልዘርዝር ።



ከእሸቴ ውሴን ቤት ወጥተው ወደ ሊቦ ሲጓዙ በየደረሱበት የሚገኘውን እስላም ጌታ ያዘዛቸውን መልእክት ለእሼቴ ውሴን እንደፈጸሙ ለሁሉም ሳይነፍጉ በስፊው እየዘረዘሩ ያስረዱ ነበር ። ጉዞዋቸውን በመቀጠል እግረ መንገዳቸውን በበለሳና በእብናት መካከል አመኖ ከተባለው አውራ ጎዳና ደንበር የሚኖሩትን የብር ኳስ የተባሉትን ክርስቲያን ቤት ተመለከቱና ከዚህ ማደር ይገባናል ብለው ድንኳን ተተከለና ሰፈሩ ።

የብር ኳስ የተባሉት ሰው በጣም ህብታም ከመሆናቸው በላይ እንግዳ በመቀበል የታወቁ ነበሩ ። ወዲያውም ለእንግዶቻቸው ቡና አስፈልተው ለቁርስ አንድ ኩንታል አተር ቢያስቆሉ ጭብጥ ጭብጥ ለማድረስ ከሰው ብዛት የተነሳ አዳጋች ሁኖ ሸህ ዘካርያስን ይህን ያክል ሕዝብ የሚከተላቸው ለምን ነበር? ብለን እንጠይቅ ይሆናል ። እኒህ አብይ ሰው የሚከተለው ሲናገር ለጆሮ እየጣፈጠ የማይሰለች እንደበታቸው ቃሉ ከአምላክ ሆኖ እሳቸው በአድራሽነት የተሾሙ መሆናቸውን ሕዝቡ ስለተረዳው ወደ ቤታችሁ ተመለሱ ብለው አሰናብተውት የነበረው ሰው ከጉዞ በኋላ በፊታቸው አልፎ ከኋላቸው ዘግይቶ ከሰፈር ላይ ሲከባቸው ያዩታል እንዲያውም ያልነበረው ተጨምሮ በርክቶ ይገኝ ነበር ።

አቶ የብርኳስም የተወደደ ተግባራቸውን የመጣባቸውን እንግዳ አቅማቸው በቻለ መጠን በማስተናገድ ሽህ ዘካርያስ የተደሰቱ መሆናቸውን ገልጸውላቸው የጧት ስግደት ጸሎታቸውን ሲፈጽሙ የብርኳስና ቤተሰቦቻቸው የሽህ ዘካርያስን የስብከት ንግግር ሰምተው ተደነቁበት ይባላል ። ምክንያቱም እስላሞች ክርስቶስንና ክርስትናን አይቀበሉም ሲባል ነበር የሚያውቁት ።

እርሱ ሲፈቅድ ግን ኃይለ መለኮቱ ፤
ሸህ ዘካርያስን አስነሳ ከቤቱ ፤
ቁርአን የተማረ ስልጡን አንደበቱ ፤
መርምሮ በማወቅ እውነትን ከሀሰቱ ፤
ገለጠው እስከመሠረቱ ፤
እስላሞች በክርስቶስ አናምንም ያሉቱ፤
እስከዚህ ነበሩ የተሳሳቱቱ ፤
በሸህ ዘካርያስ ተገለጠ እውነቱ ::
እያሉ አቶ የብርኋስ አመስግነው ሸኟቸው ::

ሸህ ዘካርያስ ከአመኖ ተነስተው ወደ ራስ ወልዴ ከተማ ሊቦ በደረሱ ጊዜ እራስ ወልዴ አንድ ሻለቃ ለአንድ ነብይ ሊያደርግ የሚገባውን አቀባበል ፈጸሙላቸው አቀባበሉም ድግስ አዘጋጅተው ሸህ ዘካርያስንና ተከታዮቻቸወን በማብላት በማጠጣት ካስደሰቱ በኋላ ከሸህ ዘካርያስ መንፈሳዊ ቃል ለመስማት ዝግጅታቸውን ገልጸውላቸው ሸህ ዘካርያስም ሳደረጉላቸው አቀባበል ካመሰገኑ በኋላ እግዚያብሔር በሶስትነቱ በአንድነቱ ተገለጸ ቁርአኑን በትክክል እየተረጎሙ እንዲያስተምሩ የላካቸው መሆኑን ስለ ራእያቸው ዘርዝረው ካስረዱ በኋላ የአምላክን ትእዛዝ አልችልም ለማለት ስለማይቻል የታዘዙትን በማስተማር በግዛታቸው የሚዛወሩና የሚያስተምሩ መሆናቸውን ተናገሩ :: እራስ ወልዴም ሸህ ዘካርያስ የእግዝያብሔር መልክተኛ መሆናቸውን በስፋው በወሬ ስምተውት የነበረውን አሁን ቤታቸው ድረስ መጥተው ዘርዝረው ባስረዷቸው ጊዜ የሸህ ዘካርያስን ገጽ እየተመለከቱ ከአንደበታቸው የሚሰሙት ቃል የሰውን ሕይወት በአንድ ጊዜ ሊለውጥ የሚችል ክባድ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ስለተረዱ እርስዎን የሚያክል የእግዚያብሔር ሰው ከቤቴ መጥቶ ሲጠይቀኝ ይቅርና ከቤተዎ እንዳሉ ቢልኩብኝ የተጠየቅሁትን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ ነበርኩ መምጣተዎም በረከት እንዳመጣልኝ አምናለሁ :: በወደዱት ስፍራ እየተዘዋወሩ የተላኩትን መልእክት ያዳርሱ በጎደለ እኔ ልፈጽመው የምችለው ጉዳይ ካለ ለጠየቁኝ ሁሉ ዝግጁ ነኝ ሲሉ ደስታቸውን ገለጹላቸው :: የራስ ወልዴን አቀባበልና አነጋገራቸውን የሰማ እስላም ሁሉ ሸህ ዘካርያስን ሊከስ አስቦ የነበረው እስላም ሁሉ ጸጥ አለ :: ሸህ ዘካርያስም ከራስ ወልዴ ተሰናብተው ጉዞዋቸውን ሊቦ ከተማ ግርጌ በስተደቡብ ከተራራው ስር ወደሚገኘው ድቅድቅ ያለው የእስላሞች መንደር ደረጣ ወደተባለው ፊታቸውን መለሱና ተጓዙ የደረጣ እስላም የሸህ ዘካርያን ሊቦ መድረስ ሰምቶ ሙቸም ደፋር ነው ከኛም መምጣቱ አይቀርም በሰይፍ ጅሀድ እንገጥማለን አንጅ ዝም አንልም እንዳይመጣብን ብለው እንደፎከሩ ሸህ ዘካርያስ ሰሙ :: እሳቸውም አብሮን የሚጓዘው አምላክ በግርማው ይበትናቸዋል ከፊታችን የሚቆም የለም ብለው ከሊቦ ወደ ደረጣ በተጓዙ ጊዜ እንደተናገሩት ደረጣ ሲደርሱ ለጅሀድ የወጣው ሁሉ ወደ ጎንደር ሲገሰግስ ታየ የደረጣ ሰላማዊ ሕዝብ ግን በሰላም ተቀበላቸውና ሰፈራቸውን ከታላቁ መስጊድ አድርገው ከሌው ተነጠፈና ለስግደት አዛን ሲያደርጉ የተከተላቸው አዛውንት ሁሉ ተማሪያቸውም ጭምር በአንድ ጊዜ ሲንበረከክና ሲሰግድ የደረጣ ሰው ተመለከተና የዘካርያስን አካል አንድ ጊዜ ለጥይት አንድ ጊዜ ለሰይፍ የሚመኙቱ በምን ጥፋቱ ነው እንዲህ አላህን አክብሮ የሚያስከብረውን አብይ ሰው ነው ለካ እንግደለው እያሉ የሚመክሩበት ዘካርያስን መጥላት አላህን ከመጣላት ይቆጠራል እያሉ ይገረሙ ጀመር :: ከስግደት በኋላ የደረጣ ሕዝብ ሸሽት ጀምሮ የነበረው አንዳዶች አምርረው ጎንደር ሲደርሱ በሳም

መሆኑን እያዳመጡ ገሚሶቹ ተመልሰው ወደየ ቤታቸው መጡ ። ሸህ ዘካርያስም ስርአታችንን እፍርስሀል ሃይማኖታችንን ለውጠሀል ትሉኛላችሁ አሉ፡ እስቲ ማስረጃ ስጡኝ ። እኔስ አንድም ስርአት አላፈረስኩ ሃይማኖትም አለወጥሁ ቁርአኑም ተሁራቱም እሪቱም/ ዘብሩ /መዝሙሩም/ ኢንጂሉም/ ወንጌሉም ይኸውላችሁ እያነበባችሁ እየተረጎማችሁ የለወጥሁትን ስፍራ ብታሳዩኝ በበደልሁ ልካስ ዳሩ ግን እላንት እራሳችሁ የተጻፈውን ትታችሁ በልበ ወለድ ለስጋችሁ የሚመቻችሁን እየሰራችሁ ዘካርያስ ሃይማኖት ለውጧል ስርአት አፍርሷል እያላችሁ ብታወሩ እግዚያብሔርም ሆነ ሰው አይቀበላችሁም ። እያሉ የተጣለባቸውን አደራ መልእክታቸውን በብዙ መቶ ለሚቆጠረው ሕዝብ አስተማሩ ። ከጸሎትና ከስብከት በኋላ ሰው ሁሉ መስጊዱና ከመስጊዱ በውጭ ጸጥ ብሎ ተቀምጦ ሳለ ከተማሮቹ አንዱ ወይ እየሱስ ወይ እየሱስ እያለ በጩኸት ድምጽ ካሰማ በኋላ ያንተ ነገር በጣም አስቸገረ ዳሩ ግን ሰማይ ምድርም እንኳ ያላንተ አልሆኑም ብሎ ተናገረ ። ሸህ ዘከርያስም ይህ ወጣት የተናገረውን ሰማችሁ አሉና ይህን ትክክለኛ መንገድ ተውራትም መዝሙርም ነበያትና ኢንጀልም የመሰከሩትም ቁርአንም ከነሱ ልዩነት የለኝም የሚለውን ቃል እንዳታጡት ፈልጉት ታገኙታላችሁ ባትፈልጉ ግን ትጠፋላችሁ ያለብኝን ሃላፊነት ሽክሜን አውርጃለሁ አሉና ተናገሩ ። የተሰበሰበው ሕዝብ ከሰማነው አንድም የሚነወር ነገር የለበትም እያለ አመስገነ ። በዚህ አይነት እያስተማሩ ከሊቦ እስከ ደንቀዝ አልፈው በበለሳ ዙረው ወደመልዛ እና ወደ እብናት ወደቤታቸው ተመለሱ በዚህ ጊዜ በመላ በጌምድር ዝናቸው ተሰማ ።



ከቤታቸው ለጥቂት ጊዜ እንደቆዩ በጎንደር ከተማ ያሉት እስላሞች እንደመጣ መጥቶ ጎንደር ሳይደርስ የተመለሰው ጎንደር ቢመጣ እንደሚሞት ስለተረዳው ነው እያሉ ሲፎክሩ እንደ ነበር ነገሯቸው ። ሸህ ዘካርያስም ጉዟቸውን ወደ ጎንደር እንደሚያደርጉ ካቀዱ በኋላ ለተከታዮቻቸው ገለጹላቸው ። ወዲያው ዝግጅት ሆነና በለሳን አቋርጠው በደንቀዝ አድርገው ወደ ጎንደር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው አሁንም ከስስት መቶ በላይ የሚሆን ሕዝብ ተከትሏቸው መምጣታቸውን በጎንደር ከተማ የሚገኙ እስላሞች በሰሙ ጊዜ በጣም ሽብር ሆነ በሰይፍ በጠበንጃ በጅሀድ እንገጥማለን ያሉት ሁሉ የሸህ ዘካርያስን መምጣት በሰሙ ጊዜ እየወጡ ጭልጋ ተጓዙ ። ደፋሮቹ ግን ቁመው ቆዩ ። ጎንደር ከተማ በገቡ ጊዜ አለቃ ገብረእግዚአብሔርና አቶ ጌታሁን ወንድማማቾች ከጎንደር ሄደው ከሸህ ዘካርያስ ጋር ሁነው ከተማሩ በኋላ የላቸው ደጋፊ በመሆን አብረው መጥተው ስለነበር ሸህ ዘካርያስም ከነ አለቃ ገብርእግዚአብሔር እጥር ግቢ ሰፈሩና በእስላሞች ዘንድ የተወሰነውን የጸሎት ጊዜ ሸህ ዘካርያስ አክብረው አዘን አድርገው ለስግደት ሲነሱ ተከታዮቻቸው ሁሉ አብረው ሲሰግዱ በቀን አምስት ጊዜ ሳያቋርጡ የሚፈጽሙትን ጸሎት የተመለከተ እስላም ሁሉ ዘካርያስ ጥፋተኛ ነው የሚሉት ከምን ላይ ነው ጥፋቱ እያሉ መጠያየቅ ጀመሩና ቀስ በቀስ አገር ሰላም ሆነ ።

ሸህ ዘካርያስም በጎንደር ከተማ እስላም ሁሉ ጌታ የሰጣቸውን እውነት በጥብቅ ለበኩለት ሕዝቡም በደስታ እየሰማ ሲያመስግን ከሰነበተ በኋላ በሄዱበት አኳኋን ተመልሰው ወደ ቤታቸው ደረሱ ።

## *ምእራፍ 12*

## *የሸህ ዘካርያስ ራስ ጉግሳ ላይ መክሰስ*

ለጥቂት ጊዜ እረፍት ካደረጉ በኋላ ሸህ ዘካርያስ እንደገና ከልጭ ተነስተው በእብናት አድርገው ሀሙስ ወንዘን እቋርጠው ፋርጣን፣ አሞራገደልን፣ የናታቸውን እገር ምክሬን፣ የተወለዱበትን ጋይንትንና ነገላን እየተዘዋወሩ ያስተምሩ ነበር ። በጌምድርን ራስ ጉግሳ ተሹመው በመጡ ጊዜ መቀመጫቸውን ሊቦ በማድረግ ፌንታ ፋርጣ በሚገኘው ከተማ ደብረታቦር ስላደረጉ ወደ መንጎዘር ኑዋሪ የሆኑት ሸቴ ዘይኑና ሸህ ይብራሂም ሸህ ሙሐመድ ዲና የተባሉት ሰወች ከደጋፊወቻቸው ጋራ ለመተያያ የሚሆን ትልቅ ሰጋጃ ምንጣፍ ከምጽዋ አስመጥተው እንዲሁም አያሌ የጎሽ ዋንጫወች ከከፋ አስመጥተው ሌላም እያሌ የጅ መንሻ ወርቅ ጨምረው ወደ ደብረታቦር ሄደው ሸህ ዘካርያስ የተባለ ሰው ተነስቶ እስላም አይሉት በእስላም ደንብ አይተዳደር ክርስትያን አይሉት ክርስትና አልተነሳ በጣም አስቸገረን እና ይህን ተግባሩን ቢያግዱልን የሱን አስተማሪነት አንቀበልም በጃችን ሳይጠፋ እሰዎ እንዲያግዱልን ልመናችን እናቀርባለን አሉና ጮሁ ። ራስ ጉግሳም የበላ ዳኛ የወጋ መጋኛ አንድ ነው እንደሚባለው ሁሉ ጉዳያችሁን እሁን እፈጽማለሁ ብለው ተስፋ ሰጥተው ሸህ ዘካርያስን በተሎ አስጠርተው እያሌ መስቀለኛ ጥያቄ እየጠየቁ ሸህ ዘካርያስን እስጨነቋቸው ። ሸህ ዘካርያስም ከአደባባይ ላይ ለተጠየቁት መስቀለኛ ጥያቄ የሚገባውን መፍትሄ የሆነ መልስ ከመንፈስ ቅዱስ እየተቀበሉ እንደመለሱ ራስ ጉግሳ እስኪሰማቸው ድረስ አስደነቃቸው ። ሸህ ዘካርያስ ከራስ ጉግሳ እደባባይ ሲመለስ ፊታቸው የሀዘን ስሜት ይነበብበት ነበር ። እለቃ ታየ የተባሉ ሊቀ ሊቃውንት ተመለከቱና ሸህ ዘከርያስን ምነው ፊተወን ከፋው ? ብለው ጠየቋቸው እሳቸውም የጌታን መልእክት እንቅፋት ሲገጥመው እየታየኝ ነው እሉ ። እለቃ ታየም ጥይት የጎረሰን ጠበንጃ ምላጩን



ቢስቡትና ሰው በእጅ አፈሙዙን ቢከድነው ጥይቱ ሰባብሮ ይሄዳል እንጅ ገትቶ ሊያስቀረው እንደማይችል የእግዚአብሔርን ቃልም የሰው ኃይል ሊያስቀረው አይችልም ። ስለዚህ የያዙት እውነት ነውና ይግፉበት እይዞዎት ብለው አጽናኑዋቸው ። በሚቀጥለው ቀን ራስ ጉግሳ ሸህ ዘካርያስን ጠርተው ለመሆኑ የምታስተምረውን ማነው ላንተ ያስተማረህ ? ብለው ጠየቋቸው ። ቁርእን ያስተማሩኝ ሸህ ኡመር ናቸው ። ትርጉሙን ግን እምላክ ገለጠልኝ ሲሉ ቢመልሱ አምላክ እንደገለጸልህ ምን ማስረጃ አለህ? አሉና ጠየቋቸው ። ይህንስ የነቢያት የሐዋርያት ይብቃኝ ። ለሙሴ ጌታ በተገለጸ ጊዜ አስረጅ የሚሆኑ ሌሎች ሰወች አብረውት አልነበሩም ። አኔስ ከጌታ ለመላኬ የአስራሦስት አመት ስራየ ምስክር ነው እንጅ ሌላ ማስረጃ እላቀርብለወትም ። ደግሞም የማስተምረው እራሱ ቁርአን የሚመሰክርላቸውን የብሉይና የሀዲስን ትምህርት ነው ። ስለዚህ እንደጥፋተኛ አልቆጠርም ብለው መለሱ ። ራስ ጉግሳም ስለ ብሉይና ሀዲስ ኪዳን ቁርአን ምን ይላል ? ብለው ጠየቋቸው ሸህ ዘካርያስም ቁርአኑን ገልጸው በገጽ 78 ምእራፍ 5 አል ሚእዳህ ክፍል 6 አንቀጽ 68 እላንት የመጻሐፍ ባለቤቶች ሆይ ተውራትንና ኤንጂልን ከጌታችሁ ወደናንተ የወረደውን እስከምታቆሙ / እስከምትሰሩባቸው / ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው ይላል በተጨማሪም በገጽ 14 ምእራፍ 2 አልበቅራህ ክፍል 1 አንቀጽ 136 በዚያም ሙሴና ይሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን እመን ይላል ። እንዲሁም በገጽ 10 ምእራፍ 2 አል በቅራህ ክፍል 1 አነቀጽ 93 በእሬት ሕግ እንድትሰሩ እያለ እሱ ቁርአን በብሉይ በአዲስ እንዲሰራ ካዘዘ በኋላ ቃሉን እርሱ ያፈረሰና ጥንትም ለአንዱ አዳም አንዲት ሄዋን በመፍጠር ምሳሌ

ያሳየውን ኳላም ወንጌል በአንዲት ሚስት መጽናት የሚገባ መሆኑን ሲያስተምር ቁርአኑ ደግሞ ከነሱ አልለይም የሚለው አንድ ወንድ አራት ያግባ አራት ሴቶች ግን ለአንድ ወንድ ብቻ ይሁኑ የሚል ተጽፎበት ይገኛል እያሉ አራት ሚስት ለማግባት ይቻላል ብለው ያስተምራሉ ገጽ 51 ምእራፍ ሶስት አልኢምረን ክፍል 4 አንቀጽ 3 ከሴቶች ለናንተ የተዋበችላችሁን ሁለት ሁለት ሶስት ሶስት አራት አራትም አግቡ ይላል ። ይህንን መሰረት በማድረግ አራት ፈቅዷል እያሉ የሚያስተምሩት ቀጥሎ ያለው መስመር ግን አለማስተካከል ብትፈሩ አንዲትን ብቻ የሚለውን ማንበብ እና ማስተዋል ይገባ ነበር ። ኃጥያት ሁሉ ባለ መፍራት የሚፈጸም በአምላክ ላይ ማመጽ ነው። እኔም የማስተምረው ይህንና ይህን የመሰሉትን አመጽ ለማስቀረት ሲሆን አያሌ ባለስልጣኖች በዋግ በላስታና በትግሬ በበጌምድርም ለማስተምረው ተግባሬ ደጋፊና እረዳት በመሆን ሲረዱኝ እርሰወ ግን አምላክ በሶስትነቱ ደግሞም በአንድነቱ ተገልጾ ያዘዘኝን ስራ አግዳለሁ ቢሉ ኃላፊነቱ የራስዎ መሆኑን እገልጽለወታለሁ ብለው በሰፊው አስረዱ ። ይህን በሚናገሩበት ጊዜ የተገኙት መኳንንት ሁሉ ለራስ ጉግሳ ይህን የመሰለው ተግባር የሚደገፍ እንጅ ሊታገድ አይገባውም ሰላሏቸው የሸህ ዘካርያስም ትምህርት የወደደ ይቀበላቸው የጠላ ይተወው ሌሎችም የእስላም ሸሆች አራት አግቡ እያሉ ሲያስተምሩ እንዲያስተምሩ ሲፈቀድ ሸህ ዘካርያስ ባንዲት ጽኑ ብሎ ሲያስተምር ሊታገድ የማይገባ ነው። ቢታገድ ግን አብይ ስተት ነው ። ስለዚህ እንዳያስተምር ሊታገድ አይገባም እያሉ ይተቻቹ ጀመር ። ራስ ጉግሳም አክለው ለመኃፋት ደጋፊ ባለማግኘታቸው እነሸህ ዘይኑን ለማስደሰት ያህል አሁን ጊዜው የሰኔ ማለቂያ ሐምሌ ተጋባት ነው ። እንዳላከራክራችሁ ስለክረምቱ ውሃ ሙላት ቀጠሮውን ለመስቀል ቀጥሬዋለሁ በቸር እንክረም በዚህ አረጅም



ጊዜ እኔም ነገሩን በሰፊው አጠናዋለሁ አንተም እዚህ ብትከርም ግጭት እንዳይፈጠር ወደ ትውልድ ቦታህ ወደ ነገላ ብትሄድና ብትከርም ደግ ነው ብለው አሰናበቷቸው ። ሸህ ዘካርያስም በነገላ በላስታ በጣርና ያሉትን ዘመዶቻቸውን አያሌ ጊዜ ተለይተው በመቆየት ናፍቀው ስለነበር ላስታ ተሻግረው ከወንድሞቻቸው ከአቶ ዋሴና ከአቶ ይሳ ጋራ ከረሙና ወደ ደብረታቦር ለመሄድ ሲነሱ ንዳድ (ወባ) ይዟቸው ታመው በቀጠሮው ለመስቀል ሳይደርሱ ቀሩ ። በዚህ ጊዜ በቀጠሮው ሸህ ዘካርያስ ቀረ ብለው እነ እሸቴ ዘይኑ አመለከቱ ሸህ ዘካርያስ ቢቀሩም ደጋፊወቻቸው እነባሻ ጠቋሬ እነ መሐመድ አማኔ ቀርበው የቀሩበት ምክንያት በመታመም መሆኑን ልከውብናል አሁንም የታመመ ይዳን የዘመተ ይግባ ነውና ደንቡ ቀጠሮ ይለወጥልንና እናቀርባቸዋለን ብለው አመለከቱ ። ራስ ጉግሳም ቀጠሮውን ለውጠው ወዲያው እንደዳነ እንዲመጣ ብለው አዘዙ ።

ሸህ ዘካርያስም ወዲያው በነ ሲሆኑ ደጋፊወቻቸው ሁሉ በነገላ፣ በመና መቀጣዋ፣ በመልዛ፣ በብናት፣ በበለሳ፣ በቋሊሳ፣ በፋርጣ፣ በጋይንት፣ በውዶ፣ አሞራ ገደል፣ በእስቴ፣ በምክሬ፣ ባፈረዋናትና በደራ የሚገኙ ሁሉ ደብረታቦር ላይ እንዲገናኙ መልክት ልከው በዋግና በላስታ የሚገኙትን አስከትለው ከጣርና ገስግሰው ጥቅምት መባቻ ደብረታቦር ከተማ አጠገብ አደም ጎጥ ላይ ከነጋድራስ ኃይሉ ቤት ደረሱ ። በናፍቆት ሲጠብቅ የነበረው የሸህ ዘካርያስ ተከታይ ሁሉ ገጻቸውን በተመለከተ ጊዜ በደስታ ረካ ። ታመሙ ሲባል የሰማው ሁሉ ቢሞቱ ማነው መልስ የሚሰጥ ? እያለ ሲጨነቅ በመድረሳቸው ለደስታቸው ወሰን አልነበረውም ። ነጋድራስ ኃይሉ ጌታ የሰጣቸው ባለጸጋ ስለነበሩና እንደዚሁም በሸህ ዘካርያስ ትምህርት

የተደሰቱ ብዙ ሐብታም ነጋዴወች ተረዳድተው ስፊ ድግስ ተደግሶ ፍሪዳ ታርዶ ከተበላ ከተጠጣ በኋላ ሕዝቡ እንዲሰበሰብ አደረጉና ለተሰበሰቡት አዛውንት ሽማግሌዎች እንዲህ ብለው ተናገሩ ንግግራቸው ምርር ያለ ኃይለኛ ተግሳጽ ነበር ።

አሁን እኔ ሞቸ ቀርቸ በነበር አሰራራት አመት ሳስተምር ከቆየሁ በኋላ ማን ዋቢ ይሆናችሁ ነበር መታመሜን ስትሰሙ ዋቢ አለን ብላችሁ ቀጠሮ የተቀበላችሁ እኔ ሳስተምር የሰማይ አምላክ ዋቢ ነው አልኳችሁ እንጅ እኔ ዋቢ ነኝ ብየ አስተማርኩ ወይ ? ዳሩ ግን እናንት አዛውንቶች ለምን ትፈራላችሁ እላንት ብትፈሩ የላንት ልጆች የማይፈሩ አሁን ይነሳሉ አሁን የላንተ በቅሎ ሳቢ ሆነው ከዚህ ያሉ ልጆቻችሁ እኔ የጀመርኩትን ስራ እነሱ ይፈጽሙታል ይኮራሉ ብየ ነው እንጅ በስማቸው እጠራ ነበር ፀሐይ ሳለች ጨረቃ ማብራት አትችልም ፀሐይ ስትገባ ግን ጨረቃ ታብራለች እንደዚሁም እኔ ሳለሁ እነሱ አይነሱም እኔ ስታጣ ግን እነሱ ይወስዱታል ይፈጽሙታል ። ብለው መርምሩ ተማሩ በመልካሙ ተያዙ እኔ በመካከላችሁ ካለሁ አልለያችሁም አሁንም ለመጣንበት ተግባር ሁላችንም በአንድነት እንመለክራለን ። ብለው ካስጠነቀቁ በኋላ ወደ ራስ ጉግሳ አደባባይ ወጥተው መምጣታቸውን ገለጹ ።

ራስ ጉግስም ከሳሾችን አቶ አሸቴ ዘይኑን ሸህ ይብራሂምን ሸህ መሐመድና ደጋፊወቻቸውን አስጠርተው ወዲያው ጉባኤ ሰብስበው አሁን ክሳችሁን እንደገና አሰሙ ነገሩ ውሳኔ እንዲያገኝ አሉ ። ከሳሾችም ክሳቸውን እንደሚከተለው አድርገው አቀረቡ ። ሸህ ዘካርያስ እስላም እንዳንለው ሸርያችን /ሕጋችን/ ያፈርሳል ክርስትያን እንዳንለው አልሃምድሊላሂ ይላል የላስታን የዋግን የትግሬን እስላም ሁሉ ሲበጠብጥ ኑሮ እነሱ ሲያባሩት በጌምድር ተሻግሮ ይበጠብጠናል ። እኛ የምንለምነው አሁን ከማስተማሩ ታግዶ እስካሁን ያልታዘዘ በመስራቱ ጥብቅ ቅጣት እንዲቀበልልን ነው የምናመለክተው ብለው አቤቱታቸውን አሰሙ ።

ሸህ ዘካርያስ መልስ እንዲሰጡ በታዘዙ ጊዜ መልስ ሲሰጡ የእስላም ሰው ስራሽ ሕግ ባፈርሰው እንዲፈርስ አስፈላጊ ነው አምላክ ያዘዘውን ግን አጸናለሁ እንጅ አላፈርስም አልሃምድሊላሂ ብልም አምላኬን ማመስገኔ ነውና አያስነውረኝም ስለኔ ጉዳይ ምን ያገባችኋል በግል ሕይወቴ ላዝበት ነጻነት የለኝምን ? የላስታን፣ የዋግንና የትግሬን እስላሞች ምን ብየ በጠበጥሁ ? በጠበጡኝ እንጅ ፤ ከሰሱኝ እረታኋቸው ። እላንትም ከሳችሁኛል እረታችኋለሁ ። መቸም እውነት ሲመጣ ለሀሰት ስፍራ የለውም ሲሉ ከመለሱ በኋላ ያልታዘዘ በመስራቱ ይቀጣል የሚሉት እኔ የቱን ነው ያልታዘዘ የሰራሁት? ያልታዘዘውን የሚሰሩት እነሱ ናቸው ። ምክንያቱም ወንጌልና ኦሪት አንዱን ፈትቶ ሌላውን ማግባት ከአመንዝራ ይቆጠራል ዳሩ ግን ቢታረቁ መልካም መሆኑን ሲናገሩ እነሱና ቁርአናቸው ወንጌልም ሆነ ኦሪት የጌታ ቃል ናቸው በነሱ ሕግና ስርአት ተዳደሩ ይሉና እንደገና ባልና ሚስት ሶስተኛ ጊዜ የተፋቱ እንደሆን ሴቷ ሌላ ወንድ አግብታ ፈትታ ከዚያ በኋላ ሊታረቅ ይችላል እንጅ ሌላ ሳታገባ የተፈታ ባል ሊታረቃት አይችልም የሚል ከብሉይ ከሀዲስ የማይስማማ ሕግ አላቸው ገጽ 24 ምእራፍ 2 አልብቅራህ ክፍል 2 አንቀጽ 230 ተመልከት ይህና ይህንን የመሳሰሉ ሕገ ወጥ ስራ የምትሰሩ ሳትታገዱ እኔ የሕያው አምላክ አገልጋይ የምሰራውን ጠንቅቄ አውቄ እማስተምረው እንደምን እታገዳለሁ አስተምራለሁ እንጅ ። ያልታዘዘ የሚሰራ ይቀጣ ካላችሁ ያልታዘዘ

የምትሰሩ እላንተ በመሆናችሁ ቅጣት የሚመለከተው እላንተን ነው ሲሉ መለሱ ።

ራስ ጉግሳ በደብረታቦር አካባቢ የሚገኙትን መጽሐፍ አዋቂወች ሁለቱ የመረጧቸውን ግእዝና አረብኛ እንዲሁም እማርኛ የሚያነቡና የሚተረጉሙ ሊቃውንት አስጠርተው በሊቃውንቱ አማካኝነት ጉዳዩ ከተጠና በኋላ ተከሳሹ ሸህ ዘካርያስ ምንም ጥፋት የለለባቸው መሆኑ ተረጋግጦ እንዲያውም ተከሰው በመቅረባቸው በመልሰ አሰጣታቸውና በአንደበታቸው ጸጋ የመላባቸው የእግዚያብሔር ሰው መሆናቸውን ከእደባባዩ የተሰበሰበው ሕዝብና መኳንንት ሊቃውንት ከእሁን ቀደም ያላወቃቸው እንዲያውቃቸውና እንዲያከብራቸው የሚገባ መሆኑን ሁሉም ስለተረዳው ሸህ ዘካርያስ የተከሰሱበት ክስ ውድቅ ሆኖ በነጻ ይሄዳሉ እንዳያስተምር ይታገድልን ሲሉ ያመለከቱትም አላግባብ ስለሆነ ሸህ ዘካርያስ በወደዱት ስፍራ እየተዛወሩ ቢያስተምሩ ሊታገዱ አይገባም ስንል ተስማምተን ወስነናል ሲሉ ወንበሮቻቸውና መኳንንቶቻቸው ወሰነው ፈረዱና ከሳሽ ተከሳሽ ተሰናበተ ።



# ምእራፍ 13

## ይግባኝ ወደ አዲስ አበባ

በዚህ ጊዜ በትግሬና በላስታ የተረቱት ይግባኝ ብለው ስላመለከቱ በበጌምድር የተረቱት እነሸቴ ዘይኑ ይግባኝ ስላሉ ተያይዘው አዲስ አበባ እንዲሄዱ ትዛዝ የደረሳቸው መሆኑንና እርሳቸውም ለመሄድ መነሳታቸውን ለትግሬ ለዋግ ለላስታና ለበጌምድር ደጋፊወቻቸው በተሎ መልክት አስተላልፈው የተቻለውን ያህል ስንቅ አዘጋጅተው ጉዟቸውን በተሎ ለመጀመር በተነሱ ጊዜ ዘመዶቻቸው ከዛ ሁሉ ባላጋራ ወጥቶ ተመልሶ ይመጣል ብሎ ለማመን ስላዳገታቸው ደካማውና እሴት ህጻናቱ እንባ በእንባ እየተላቀሱ ሲያዩ ወንድ ወንዱ መሳሪያ ያለው መሳሪያውን እያነሳ ስለተከተላቸው እያጀባቸው ጉዟቸውን ጀምረው በሰላም በ 1898 ዓ.ም አዲስ አበባ ገቡ ። ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ሲጀምሩ እየተላቀሱ ሲሸኟቸው ከነበሩት መካከል የታናሽ ወንድማቸው የዋሴ ጀብሪል ባለቤት ወይዘሮ ምጥን እንዲህ ሲሉ ገጠሙላቸው ።

ውሸትን በአጋስስ ጭነው መጡብህ ፤
ትረታቸዋለህ አንድ እውነት ይዘህ ።
ደህና ዋል ጌታየ ደህና ተመለስ ፤
አንደበትህ ይሰላ በመንፈስ ቅዱስ ፤
አይለይህ ጌታ እስከዛው ድረስ ።
የጌታ ባለሟል ልበ ቅን ነህና ፤
በሄድክበት ጉዳይ እረተሀቸው ና ።
በጎንደር በትግሬ ዋግም ሆነ ላስታ ፤
እረታቸው እንጅ መች እርሱ ተረታ ፤
ይግባኝ ብለው ሄዱ መስሏቸው ጨዋታ ፤
አሁንም እረቶ ይመጣል የኔታ ።
ለብዙው አንዱ ቁሞ የለለው ፍራት ፤
ምንኛ ጽኑ ነው የሱ ሃይማኖት ።
በል በርታ ጌታየ አይዞህ ሁሉም ያልፋል ፤
በማይጠፋ ቀለም ታሪክህ ይጻፋል ።

በማለት ግጥማቸውን እየደረደሩ ሸኟቸው ። ወዲያውም አዲስ አበባ እንደደረሱ መምጣታቸውን ሲጠባበቅ የነበረው የእድዋ የሰቆጣ ከአራት እመት የበለጠ ለይግባኝ እይግባኝ አዲስ አበባ ሆኖ ሲጮህ በዋግና በሰቆጣ በትግሬ በአድዋ በበጌምድር በደብረታቦር ለአሰራ አምስት አመታት ለተደረገው ክርክር ሲረታ የኖረው የሸህ ዘካርያስን መምጣትና አዲስ እበባ መግባት እንደሰማ ብርክና ድንጋጤ እያደናገረው ሸህዘካርያስን እይቶ የማያውቅ ፊታቸውን ለማየት ብቅ ጥልቅ ይል ጀመር ። እሳቸውም 30 በሚሆኑ የጦር መሳርያ የያዙ ወንድሞቻቸው ታጅበው ከመቶ በላይ የሚሆኑ ደጋፊወቻቸው ተከበው ሳይን እሩቅ ሆኑባቸውና ሲቸገሩ የነበልባል ሰይፍ መስለው ሰለታዩዋቸው ይግባኝ ባዮች በእዲስ አበባ ያለውን በእስልምና ሃይማኖት የሚመራውን አረብና ቱርክ ህንድና ጉራጌ አባበሉና አንድነት ሆነው ፍርድ ይሰጠን ሲሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ለአፄ ምኒልክ አመለከቱ ።

ንጉሠ ነገሥቱም ሸህ ዘካርያስን አስቀርበው ለመጀመርያ ጊዜ ለተከሰሱበት መልስ እንዲያቀርቡ በጠየቋቸው እለት ንጉሠ ነገሥቱም ሆኑ ሸህ ዘካርያስ ለመጀመርያ ጊዜ የተያዩበት እለት ነበር ። ከአደባባዩ የሚገኘው የይግባኝ ባይ ደጋፊ የሆኑት ዘካርያስን ለመጀመርያ ጊዜ ለማየት ምቹ ጊዜ ሰለሆነላቸው በሸህ ከሚቆጠሩት እሰላሞች መካከል ክፍተኛ ክፍተኛ የሆኑት ከንጉሠ ነገሥቱ አደባባይ መቅረብ እድል የገጠማቸው ብቻ የሸህ ዘከርያስን ፊተ ገጽ ለማየት ቻሉ ።

ሸህ ዘካርያስም ወደ አደባባይ ሲገቡ ከእንድ መቶ ያላነሱ ሰወች ክብብ አርገዋቸው ከአደባባዩ ሲደርሱ እለቃ ታየ የተባሉ ታላቅ ሊቅ ቀረብ ብለው ለነአፄ ቴወድሮስና ለነ አፄ ዮሐንስ ያዳገተውን ጦርነት



እንተ መጀመርህ ያስመሰግንህል አምላክ ከአንተ ጋር ከሆነ ምንም አትሆንም አይዞህ ብለው የሚያበረታታ ቃል ሰጥተዋቸው አለፉና ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው እጅ ነሱና ቆሙ ። ሕዝብ እንዲያስተዳድር ከእግዚያብሔር አደራ የተቀበለ ንጉሠ ነገሥትና ለምትጠፋው አለም እንዲያስጠነቅቅ ስሳሜ በመንፈስ ያደረበት ነብይ ለመጀመርያ ጊዜ የተያዩበት እለት ምን አይነት ሰሜት እንደነበር ለመግለጽ እንኳን እኔ በወሬ የሰማሁት ይቅርና አብረው ከእደባባዩ ለነበሩት እንኳ ሰሜትን ለመግለጽ ሳይቸገሩበት አልቀሩም ። ከዙፋን የተቀመጠ ንጉሠ ነገሥት ግርማ ሞገስ ጸጋ መንፈስ የተጎናጸፈውን የእግዚያብሔርን መልክተኛ ሲመለከቱት በክሳሾቹ አንደበት ሲወነጀልበት የነበረው የሸህ ዘካርያስ አካል የመለኮት ስልጣን የሰፈረበት እንኳ ለባላጋራ ለንጉሠ ነገሥቱ የሞቀና የደመቀ ክብርና ሞገስ የከለለው ሁኖ ተገኘ ። በክሱ መሰረት መልሰ እንዲሰጡ ከተነገራቸው በኋላ ቀጠሮ ተቀብለው እጅ ነስተው ተመለሱ ።

## *ምእረፍ 14*

## *ታላቁ ጉባኤ*

በቀጠሮው ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ሰፊ ጉባኤ እንዲደረግ ጥብቅ ትእዛዝ እስተላለፉና አቡኑ፣ ሊቃውንትን፣ ወንበሮችን፣ እፈ ንጉሶችን፣ ሽማግሌዎችን፣ መሳፍንትንና መኳንንትን ሰብሰበው ለጉባኤ ተቀመጡና ከሳሾች ክሳቸውን አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ በአደባባዩ የቀረበው ሕዝብ እጅግ ብዙ ስለሆነ ብርቱ ቁጥጥር ተደርጓል ። የቀረበው ክስ ሃይማኖታችን ለውጧል ሰርአታችንን አፍርሷል ብለው ነበር ። በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክ ይህን የሃይማኖት ጉዳይ በዳኝነት ለማየት የተገደዱበት እስላም ከእስላም በሰተጣሉ ለማስማማት ነበር ። ዝም ብለው ቢተዋቸው ችግር የሚፈጠር ስለሆነ ሰላም እንዲፈጠር ጉባኤው ተከፈተ ። ተከሳሹ ምን ብየ ነው ሃይማኖት የለወጥሁ ስርእትስ ያፈረስሁ? ብለው ከሳሾችን ሰለጠየቁ ይግባኝ ባዮች እነ ሽህ እደም፣ እነ እሸቴ ዘይኑ፣ እነ ሽህ ይብራሂምና እነ ሽህ ሙሐመድ ዳና መልስ ሳይሰጡ እንድ የአረብ መሀንዲስ መናገሻ ቅዱስ ጊወርጊስን ለመስራት የመጣ ብድግ አለና እላህ እራት ሚስት ቢያዝልን አንተ አንዲት ትበቃለች እያልክ ነው ስርአታችንን ያፈረስክ ብሎ ተናገረ ።

የሽህ ዘካርያስ መልስ ። ከጥንቱ አምላክ ሲፈጥር ለእንድ አዳም አንዲት ሂዋን ብቻ ፈጠረ እንጅ አራት ሂዋን እልፈጠረለትም ይህም በወንጌል ማቴወስ ምእራፍ 19 ቁጥር 3 እስከ 9 ሲነበብ ለእንዱ አዳም አንዲት ሂዋን ብቻ መሆኑዋንና ሊፋቱም የማይገባ መሆኑን ያስረዳል ይህንን በብሉይና ሀዲስ እራትና ወንጌልን እንድንሰራበት እንደ ሕጉም እንድንተዳደርበት ቁርእኑ በገጽ 78 ምእራፍ 5 እል ሜሶዳህ ክፍል 6 እንቀጽ እንዲህ ይላል እላንት የመጽሀፍ ባለቤቶች ሆይ ተውራትና ኤንጂልን ከጌታችሁ ወደላንት የወረደውን እስከታውቁ / እስከምትሰሩባቸው / ድረስ በምንም ላይ እይደላችሁም በላቸው ። የእራት የወንጌል ቃል እውነት



ነው ስሩበት የሚለው ቁርእን እራት አግቡ ቢልም ብትፈሩ እንዲት ብቻ በላለ በአንድ ጽኑ ብየ ባስተምር እንደ ትእዛዝና ስርአት አፍራሽ እያስቆጥረኝም ። ጉዳዩም በትግስት ሰናጠናው ስርእቱን ከህይወት ሰናዋህደው አንድ ወንድ እራት ሲፈቀድለት አራት ሴቶች አንድ ባል ይበቃችዋል ያለው ሰው እንጅ አምላክ ለእንዱ አንዲት ብቻ ነው የፈቀደለት ። ዛሬም ቢሆን በምድር ላይ ሰለሚወለዱ ወንድና ሴቶች የተመጣጠነ ሴትና ወንድ ነው እንጅ ለየእንድ እንዱ ወንድ አራት እጥፍ ሴቶች እይወለዱለትም ይህ ከእንድ ቤት በመቀመጡ እሰደሳች ነው ተብሎ ሲታሰብ እራቱ ሴቶች በእንድ ወንድ ቅናት ዱላ ሲማዘዙ እነሱን ለማስማማት ብትር ይዞ ሲከላከሉ ከመኖር በስተቀር ደስታን ሊገልጽ አይችልም ። ሚስቶችን ብንበድልም ብእድ ናቸው ብለን እናትና ልጆቻችን እህቶቻችንም ለእራት እንድ ይድረሳቸው ማለታችን እንደምን ተዘነጋ ። ይህ አምላካዊ ያልሆነ ሰው ሰራሽ ቆራጥነት እይደለምን ? ይህንና ይህን ስርአትና ሃይማኖት እኔ ያፈረስኩትና የለወጥኩት ሳይሆን ጥንትም ቢሆን የአምላክ ፈቃድ አለመሆኑን እንኳ የተቀባው ንጉሥ ማንም ሊገምተው የሚችል ነው ። ግርማዊ ሆይ ፍርድ በራስ ሊጀመር ይገባዋል እስኪ እንዲት ሚስት ለእራት ወንዶች ትብቃ ብሎ ሕግና ስርአት ይውጣና ወንዱ ሰጋ እንዳየ ድመት ተናንቆ ያላለቀ እንደሆነ ይታይ በራስህ የምትጠላውን በሰው አታድርግ ያለውን የወንጌል ቃል መሰረት በማድረግ እንዲት ለአንድ ትበቃለች ብየ እስተምሪያለሁ ይህ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ከማስተማር ታግዶ በስርአት አፍራሽነቱ በሞት ይቀጣል ብለው እነሽህ አደም ሰቆጣ ላይ ቢከሱኝ እንዲሁም ደጋፊወቻቸው እነአህመድ ዲን ትግሬ ላይ ቢከሱ እኔንም በጌምድር ከራስ ጉግሳ ላይ እነእሸቴ ዘይኑ እነሽህ ይብራሂም እነሽህ ሙሐመድ ዳና ቢከሱኝ ዳኛ

የድህ መዳኛ ስለሆነ ክሳቸው ውድቅ ሆኖ እኔም በነጻ ተለቅቄ በተግባሬ እንድቀጥል ስለተፈረደልኝ በይግባኝ የመጡበት ምክንያት ይህ ነው ። አሱና የሚያስተምሩበትም በአረብኛ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአኑ ከንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን ስር አስቀምጠው የሰጡሁት ሁሉ መልስ ይኸው መጽሐፉ ሊቃውንት እየመጣ እያነበበ እየተረጎመ ለግርማዊነተዎ ያስረዳ ። የቁርአኑ መጽሐፍ በአሪት ሕግ ስሩ ይሳል ገጽ 10 ምአራፍ 2 አል ብቅራህ ክፍል 1 አንቀጽ 136 በዚያም ሙሴና ይሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን እመን ። ሲል እኔም እንደ ቁርአኑ ቃል ኦሪትን መዝሙርን ነቢያትንና ወንጌልን እስከመልክቱ ለአሰራአምስት አመታት አስተምሪያለሁ ለወደፊቱም እስከለተ ሞቴ እንዳላስተምር ሊያግደኝ የሚገባው የለም ምክንያቱም የማስተምረው እንደፈጣሪ ቃል ጠንቅቄ ጠብቄ ስለሆነ ነው ሲሉ ከተናገሩ በኋላ ፍጆታውን ለነ ሸህ አደም ሰጡ ።

በይግባኝ ከሳሾች አንዲት ትበቃለች የሚለው ታጥሯል ሊነበብና ሊተረጎም አይገባም አሉ ደግሞም አለማስተካከልን ስትፈሩ ነው የሚል ስለዚህ ለሁሉ በቂ ሐብት ኑሮት አስተካክሎ ለመያዝ ከቻለ አራት ከማግባት አያስከለክለውም አሉና መለሱ ።

መልሰ ሰጭው ሸህ ዘካርያስ ሲመልሱ ታጥሯል ለምትሉት አጥሩን እርገጡና አንብቡት ሸህ የለውም አይወጋችሁም ደግሞም ታጥሮ የሚጠበቅ ማናቸውም ሁሉ ጠቃሚ ስለሆነ እንዲጠበቅ ይታጠራል እንጅ ዋጋ ቢስ ቢሆን ኑሮ ይደመሰስ ነበር አንጅ ታጥሮ አይጠበቅም ነበር ። አለማስተካከልን ብትፈሩ ያለውም በሀሰት አይደለም እግዚያብሔር ሐብት ያለው አራት ሲያገባ የለለው አንድ ይጣ ማለቱ ነውን ? ለሚፈራ



ቁርአኑ አንዲት ትበቃለች ብሏል ለማይፈራ ግን ክርስትያኑም ቢሆን ጓዳ ሙሉ ገረዱን ያንጋጋዋል ። አለማስተካከል ብትፈሩ ማለቱ ግን አንድ ወንድ እራሱ ለአራት ሴት ፍላጎት በቂ አይሆንም ማለቱ ነው ይህን ለማስተዋል ያዳገታችሁ ሕጉን ስታቋቁሙ ከምክሩ ሴቶች ባለመኖራቸው ችግራቸውን ሳትረዱላቸው ላራት አንድ ይብቃቸው ብላችሁ በመዶለት አሴራችሁባቸው ይህንን የሚመለከት ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ አንድ ቀን ፍርዳችሁን ይሰጣችኋል ብለው መለሱ ።

በይግባኝ ከሳሾች መልሰ ሰጭውን ባተረጓጎም ለማደናገር ስለሞከሩ ክሳሽ ተከሳሽ የመረጧቸው አረብኛ ቋንቋ ግእዝና አማርኛ አዋቂ ሊቃውንት ተመርጠው ከሳሾችን እራሳቸውን እያስነበቡ እያስተረጎሙ ንጉሠ ነገሥቱ አፄ ምኒልክ እራሳቸው በተገኙበት በተደረገው ጉባኤ ጉዳይ ከባድና ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ ከቀኑ 3 ስአት ሲሆን የተጀመረ እስከ ዘጠኝ ስአት ከተነጋገሩበት በኋላ በይደር ለሚቀጥለው ቀን ጉባኤው እንዲሰበሰብ ተነግሮት ተበተነ ። በማግስቱ ጥናቱ ቀጥሎ ዋለ ።

በይግባኝ ከሳሾች ከበድ ያለው ሸህ ዘካርያስን የከሰሱበትን ጉዳይ እንዲህ ሲሉ አመለከቱ ሃይማኖታችን የለወጠው ቁርአናችን አላህ አንድ ነው አይወለድም አይወልድም የሚለውን ለውጦ ተወለደ ሲል ያስተምራል ። እስላም ሆኖ ይህን ሊያስተምር አይገባውም ይህን ለማስተማር ከፈለገ እራሱ ክርስትና ተነስቶ ማስተማር አለበት ክርስትና የሚያስተምር የእስላም መምህር ሊኖር ይገባል ወይ ? ሲሉ አመለከቱ ።

ከአቤት ባዮች አፍ ቀበል አደረገና አቡነ ማቴወስ አስሬ አምስት አመት የብለይ የሀዲስ የመዝሙርና

የነበያትን መጽሐፍትን ሲያስተምሩ ምነው እራስዎ ክርስትያን ከመሆን ዘገዩ ? አመልካቾች እንዳመለከቱት እስላም ሆኖ የክርስትና አስተማሪስ ለመሆን መንገድ አለው ወይ? የክርስትና አስተማሪ ለመሆን በቅድምያ እራስ ክርስቲያን መሆን አያስፈልግም ወይ ? ሲሉ ሸህ ዘካርያስን ጠየቋቸው ::

መልስ ሰጭው ሸህ ዘካርያስ በቅድሚያ ለአቡነ ማቴወስ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል :: የጳውሎስ መልእክት 1 ቆሮንቶስ ምእራፍ 9 ቁጥር 3 ለሚመረምሩኝ መልሴ ይህ ነው ይልና ከቁጥር 19 እስከ 23 ክሰው ሁሉ አርነት የወጣሁ ስሆን የበለጡትን እንድጠቅም እንደ ባርያም እራሴን ለሁሉ አስገዛሁ አይሁድንም እጠቅም ዘንድ ከአይሁድ ጋራ እንደ አይሁድም ሆንኩ ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅምም ዘንድ እኔ እራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንዳለሁ ሆንሁ ሕግ የለላቸውን እጠቅም ዘንድ :: ያለ እግዚያብሔር ሕግ ሳልኖር ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደለለኝ ሆንሁ :: ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ :: በወንጌልም ማህበርተኛ እሆን ዘንድ ስለወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ :: ሲል ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደተናገረው እኔም ለሰው የምጠቅምበትን መንገድ እከተላለሁ :: የዘገየሁ ብዙወችን ለማስከተል ስለፈለግሁ ነው ስመጣም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ነው የምመጣው :: እስራአምስት አመት የኦሪትን የመዝሙርንና የነበያትን የወንጌልንና የመልእክቶቹን መጽሐፍ ባስተምር እንድንመራባቸው እንድንሰራባቸው እራሱ ቁርአን የሚያዝ መሆኑን ቀደም ብየ በጠቀስኳቸው የቁርአን ቃል ቁርአን የሚያዘውን ቃል ለማስተማር ክርስትና መነሳት አስፈላጊ አይመስለኝም:: የእስልምና ሃይማኖት መስራች በሆነው ሙሐመድ



ተጽፎ የቆየው ቁርአን ስለክርስትና የሚመስክረውን ገልጾን ብናስተምር መንገዱ ያስኬዳል ዳሩ ግን ስለክርስትና ቁርአን የሚመስክረውን ብናስተምር የክርስትያን መምህር አያስኘኝም የእስልምና መጽሐፍ የሚያስተምር የቁርአን መምህር ያሰኛል እንጅ :: ክርስትና መነሳት የሚያስፈልገው ክርስትያን ለመሆን ብቻ ነው :: ስለክርስትና ለማስተማር ግን ማናቸውም ሰው ሁሉ እውቀት ካለው ቢያስተምር ያስከለክለዋል ብየ አላምንም ሲሉ መለሱ ::

በይግባኝ ለከሰሱት እነሸህ አደም እነሸህ ሙሐመድ ዲና እነእሸቴ ዘይኑ ለጠየቁት ሲመልሱ እንደዚህ ብለዋል :: አሁንም ቁርአን አላህ አይወልድም አይወለድም ይልና እንደገና ቃሉን ለውጦ በኦሪት በወንጌል ቃል ሂዱ ክጌታ የወረዱ ናቸው ይላል ብሉይና ሀዲስ ይቆዩና እራሱ ቁርአን ስለ ይሳ አወላለድ የሚከተለውን ምስክርነት ይሰጣል ::

ማርያም ሆይ አላህ በእርግጥ መረጠሽ አነጻሽም በአለማት ሴቶች ላይ መረጠሽ :: መልአክ ያሉትንም አስታውስ :: መሪም ሆይ አላህ ከርሱ በሆነው ቃል ስሙ ኤል መሲህ ኢሳ የመሪም ልጅ በዚህ አለምና በመጨረሻው የተከበረ ከባለሟሎቹ በሆነ ልጅ ያበስርሻል :: በህጻንነቱና ባደገም ጊዜ ሰዎችን ያስተምራል ከመልካሞቹም ነው :: ጌታየ ሆይ ሰው ያልነካኝ ስሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች ነገሩ እንዲህ ነው አላህ የሚሻውን ይፈጥራል አንዳችን ባሻ ጊዜ ለሱ ሁን ይለዋል ወዲያውኑም ይሆናል አላት :: ገጽ 37 ምእራፍ ሶስት አሊኢምራን ክፍል ሶስት አንቀጽ 42 እና 45 እስከ 48 ይገኛል ::

በነብያቶች ፈለግ ላይ የመሪምን ልጅ ኢሳን ከተውረት በስተፊት ያለው አረጋጋጭ ሲሆን አስከትለን ኤንጀልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ኢሳያስ ምእራፍ 9 ቁጥር 6 ስሙ ድንቅ ይባላል ብርቱ አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ::

የጥንቶቹ መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው የኤንጀልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረድ አላህ ባወረደው ሕግ የማይፈርድ ሰው እነዛ አመጸኞች እነሱ ናቸው :: ገጽ 75 እና 76 ምእራፍ 5 አል ሚኢዳህ ክፍል ስድስት አንቀጽ 6 46 እስከ 49 ይገኛል ::

በመጽሐፍ ውስጥ መሪምንም ታሪኳን አውሳ መንፈሳችንንም ጀብሪልንም ወደሷ ላክን እሷም ሰው መስሎ ተገለጸላት እኔ ንጹህን ልጅ ለአንች ልሰጥሽ የጌታሽ መልክተኛ ነኝ አላት :: በጋብቻ ሰው ያልነካኝ ነኝ አመንዝራም ሳልሆን ለኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል አለች :: እሱም አላት ነገሩ እንዲህ ነው ጌታሽ እሱ በኔ ላይ ገር ነው በሰወችም ታምር ከኛም ችሮታ ልናደርገው ይህንን ስራን የተፈረደም ነገር ነው አለና እፍ አለባት ወዲያውኑም አረገዘች አርሱም በሆዷ ይዛው ወደሩቅ ስፍራ ገለል አለች :: ይህ የመሪም ልጅ ይሳ ነው ያ በርሱ የሚጠራበት እውነተኛ ቃል ገጽ 210ና 211 ምእራፍ 19 መሪን ክፍል 16 አንቀጽ 16 እስከ 21 ይገኛል ::

ያችን ድንግልናዋን የጠበቀችውን በአርሷም ውስጥ ከመንፈሳችን እፍ ያልንባትን እርሷንም ልጇንም እንደዚሁ ለዓለማት ታምር ያረግናትን መርያምን አስታውስ :: ይህች ሕግ ጋር አንዲት መንገድ ስትሆን በእርግጥ ሃይማኖታችሁ ናት እኔም ጌታችሁ ነኝና



ተገዙኝ :: ገጽ 227 ምእራፍ 21 አል አንቢያ ክፍል 17 አንቀጽ 91ና 92 ይገኛል ::

የቁርአኑ ቃል ከዚህ በላይ በተገለጸው ሲያስረዳ በተጨማሪም በሙሴ ኦሪት በዳዊት መዝሙር በነበያትና በወንጌል በጠቅላላው በብሉይና በአዲስ ኪዳን እንድንሰራባቸው ያዘዘ ሲሆን ዘፍጥረት ምእራፍ 3 ቁጥር 15 በአንችና በሴቲቱ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ በዘርሽና በዘሯ መካከል እርሱ እራስሽን ይቀጠቅጥሻል አንች ሽኮናውን ትቀጠቅጫለሽ :: ያለው የሴቲቱ ዘር ከማርያም የተወለደው የሱስ የባቡን የሰይጣኑን እራስ ቀጠቀጠው ሰይጣንም የየሱስን እጅና እግር አስቀጠቀጠው ::

መዝሙር ምእራፍ 2 ቁጥር 11 ለእግዚያብሔር በፍርሀት ተገዙ በእርሱም ደስ ይበላችሁ ልጁን ስሙት እንዳይቆጣ በአላችሁበት መንገድ እንዳትጠፉ ቁጣው ጥቂት ቆይታ ትነዳለችና በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው ይላል ::

እንዲሁም በኢሳያስ ምእራፍ 9 ቁጥር 6 ህጻን ተወልዷልና ወንድ ልጅም ተሰጠነ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙ ድንቅ ተብሎ ይጠራል :: መካር ብርቱም አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ይባላል ኢሳያስ ምእራፍ 7 ቁጥር 14 ስለዚህም እሱ እግዚያብሄር ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ትርጉሙ እግዚያብሔር ከኛ ጋራ ሆነ ማለት ነው ማቴወስ ምእራፍ 1 ቁጥር 23 ::

እንዲሁም በኢሳያስ ምእራፍ 53 ቁጥር 1 እስከ 12 ስለኃጢያተኞች ቤዛ ሁኖ መሞቱን ያስተምረናል በእርሱ ቁስል እኛ መዳናችንን ይገልጽልናል ።

ዳንኤልም በበኩሉ በምእራፍ 9 ቁጥር 24 እና 25 የቅዱሳን ቅዱስ መሲህና ንጉሥ ክርስቶስ ብሎ በስሙ ይጠራዋል ።

ወንጌልም እንዲሁ በዮሐንስ ምእራፍ 3 ቁጥር 16 አግዚያብሔር እንዲሁ አለምን ወዷልና አንድ ልጁን እስኪሰውጥ ድርስ በእርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጠፋ የዘላለም ሕይወት ትሆንለት ዘንድ አንጅ ። ይላል ።

ማርቆስ ምእራፍ 16 ቁጥር 16 ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል ።

ማቴወስ ምእራፍ 28 ቁጥር 19 እና 20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ አጥምቋቸውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ። በእርሱም ያዘዝኳችሁን ሁሉ ጠብቁ አስተምሯቸውም እኔም እነሆ ከላንት ጋራ ነኝ እስከፍጻሜ ዘመን ድረስ ። አሜን ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የቁርአንና የራሱ ቃልና እራሱ ቁርአን የሚመሰክርላቸው አሪት መዝሙር ነቢያትና ወንጌል እስከ መልእክቱ አወላለዱንና አምላክነቱን ስለሚመሰክሩለት ይህንን ነው ያስተማርኩት ይህንም እኔ ላልሆን እራሱ ቁርአን ሃይማኖታችሁ ይህች ናት ብሎ ስለመሰከረ አሰተማርኩ እንጅ በራሴ ስልጣን አንዳችም አለወጥኩም እነዚህ ቅዱሳን መጽሐፍት በስልጣኑ በመንፈስ መሪነት ያጻፈ አምላክ ቢልከኝ እቢ ለማለት አልችልም የምችልበት መንገድ ካለ እናንተ ፍረዱ ።



እስላም ሆኖ ይህን ማስተማር አይገባውም የሚሉኝ እስታሁንም ሆነ አሁንም ቢሆን ክርስትና ብነላ የተላከሁበትን ቁርአኑን በትክክል እየተረጎምኩ እንዳስተምር የታዘዝኩትን እንዳልሰራ እንቅፋት አንደሚሆኑብኝ ስላወቁ ስራየን ለማቆም ነው የሚጥሩ ምክንያቱም ክርስትያን ሆኘ እስላምን ለማስተማር እንደማልችል ስለሚያውቁ ነው ። ክርስትናን የሚያስተምር የእስላም መምህር ሲኖር ይገባል ወይ? ላሉት የእስልምና መመሪያ የሆነው ቁርአን የሚያዘው ከሆነ ይህን የቁርአን ቃል እኔ እስላሙ ለእስላሞች ላስተምር አዎ ይገባኛል ነው መልሴ ።

ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ከዚህ በላይ በይግባኝ ከላሾች የጠየቁትንና በይግባኝ ተከላሾች የመለሱትን መልስ ካዳመጡ በኋላ ተከሳሹን ሸህ ዘካርያስን እንዲህ ብለው ጠየቋቸው ።

አምላክ ቢልከኝ እምቢ ለማለት አልቻልኩም የምትችሉበት መንገድ ካለ እናንተ ፍረዱ ብለሀል ። ለመሆኑ አምላክ መቸ ወዴትስ ነው የተገናኛችሁና የላከህ ? ሲሉ ጠየቋቸው ።

ግርማዊይ ሆይ ግርማዊነተዎ በኢትዮጵያ ላይ በነገሡ በሶስት ዓመት 1885 ዓ.ም በላስታ አውራጃ አይና ቡግና በተባለ ወረዳ በጣርና ቀበሌ እኖር ነበር ። ስለእስልምና እውነተኛነት በጥብቅ ለመመርመር ሀሳቤን አነሳስቸ ዘወትር በግል ጸሎት ፈጣሪየን እለምነው ነበር ። አምላክም ጸሎቴን ሰማና መልስ ሰጭ የሆነው በተለይም በረማዳን ወር ጾም ውስጥ አንድ የካብ ጎጆ አሰርቸ ክሰው ተለይቸ የሱባኤ ጸሎት ለሰባት ቀናት ለመጸለይ በጀመርኩበት ወቅት ያለሁበት ቤት በልዩ ስሜት ተሞላ። አይኖቸ የሚመለከቱት እንግዳ

ነገር ሆነብኝ በዚህ ጊዜ የመጀመርያውን ራእይ አየሁ ::

አንድ ሰው ከምስራቅ ተነስቶ ሲመጣ አየሁት ይህ ሰው ቁመቱ እረጅም መልኩም የተዋበ ነው ጸጉሩን የተሰራ ከመልኩ ውበት የተነሳ በሰው ግምት አይመጠንም ነበር :: ወደኔ ቀረበና በቃሉ ዘካርያስ ብሎ ጠራኝ እኔም አቤት ስለው የእግዚያብሔር ባርያ ወደኔ ቅረብ አለኝና እግዚያብሔር በቃሉ ወዳንተ ላከኝ የቃሉን ትርጉም ግምቱን እንድታውቅ ሲለኝ እኔም እሺ እልኩት ከራሴ ላይ እፍ ቢልብኝ ከራሴ እስከእግሬ ድረስ ልዩ ስሜት ተሰማኝ :: ከዚህ በፊት ቁርአኑን የማነበው ያለማስተዋል ነበር በዚያን ጊዜ ትርጉሙ ግልጥ ብሎ ታየኝ :: እፍ ካለብኝ በኋላ በመጣበት አኳኋን ተመለሰ :: ከሱባኤው ሳልነሳ ከዚው ስፍራ እንዳለሁ አርብ ሌሊት በዶሮ ጩኸት ሶስት አዛውንቶች የተከበሩ አሁንም በሰው እገላለጽ ለማስረዳት የሚያዳግት ክብር ያላቸው እንደደናግል ያሉ መልካቸው አንድ አይነት የሆነ መጥተው ከመካከላቸው አስቀመጡኝና በቃላቸው ልጃችን ዘካርያስ ደስ ይበልህ አትዘን የትርጓሜውን ነገር ልንገልጽልህ መጥተናል ልንፈጽምልህ ነውና የበረታህ ሁን ቁርአኑንም በትክክል ተርጉመው ነገር ግን እኛም አንለይህም በኦሪቱና በወንጌሉ የቁርአኑን ቃል አይተህ አስተካክለው ካልተስማሙ ቁርአኑን አርመው :: ብለው ከተናገሩ በኋላ ሶስቱም ሽማግሌች ወደ ሰማይ አንድ አካል ሆነው ሄዱ :: ከሄዱ በኋላ ደመናና ዝናብ መጣ አመጣጡም ከፀሐይ መውጫ ነበር የሚሄደውም ወደ ፀሐይ መግቢያ ነበር በዝች አለም ላይ ነው እኔም አሻቅቤ ስመለከት ነበር አንድ አካል መልሶ ከኔ ጋር ሆኖ አገኘሁት እጄን ይዞ በቃሉ አይዞህ አንለይህም የበረታህ ሁን አለኝ :: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የምፈጽመውን ስራ የሚመራኝ ይህ



የማይለየኝ ጓደኛየ ነው :: ግርማዊ ሆይ እንዲህ በሆነ ትእዛዝ ስራውን ስጀምር ብዙ ደጋፊወችን ጌታ ስለሰጠኝ በምሄድበት ሁሉ ይከተሉኛል ከመቄት ከሸድሆ ከነገላ ከላስታ ከዋግና ከትግሬ ከለሜንና ከወልቃይት ከወገራና ከጎንደር ከበጌ ምድርም እየመጡ የማስተምራቸውን እየተቀበሉ ወደ የመጡበት ስለናኙት ዝናው በያለበት ተዳረሰ :: ወዲያውም ተቃዋሚ በመነሳቱ ሰቆጣ ከዋግ ሹም ጓንጉል ላይ ተከሰስኩ አህመዲን የተባለው ተማርየን አድዋ ከደጃዝማች ገብረስላሴ ላይ ከሰሱት ከዚያም እረትተን በጌምድር ከራስ ጉግሳ ላይ ተከለሰኩ ከዚያም እረታኋቸው በይግባኝ የመጣንበት ጉዳይ ይህ ነው ካሉ በኋላ ካሁን ቀደም እየተከሰስኩ በየመኳንንቶቹ የቀረብኩና ዛሬም በግርማዊነተዎ ፊት ተከስሸ መቅረቤ ጌታ ፈቃዱን ያልሰማ እንዲሰማ ያላወቀ እንዲያውቅ በየአደባባይ አዋጅ የሚነገርበት መንገድ ይህ ነው :: በዚህ አይነት የጌታ እቅዱ ዛሬ የተጀመረ አይደለም በነቢያትና በሐዋርያት ዘመንም በዚህ እይነት ነበር የሚፈልገውን ፈቃዱን ጌታ የሚያውጀው :: ለምሳሌ በጳውሎስ ጊዜ ሲያሳደው የነበረውን እሱ እራሱ እንዲያስተምርበት በተጠራ ጊዜ እንዲህ ይላል ገላትያ ምእራፍ 1 ቁጥር 14 እስከ 16 አይሁዳዊ ሕግም አበዛ ነበርኩ አጽንቼ ከብዙ ወገኖቸ ይልቅ እጅግም አቀና ነበር አባቶቼ ላስተማሩኝ :: እግዚያብሔር ግን በወደደ ጊዜ ከናቴ ማህጸን ያወጣኝ በጸጋውም የጠራኝ ልጁን እንዲገልጥብኝ አሕዛብን አስተምር ዘንድ የዚያን ጊዜ አልተማከርኩም ከስጋና ከደም ጋር ::

የሐዋሪያት ስራ ምእራፍ 9 ቁጥር 15 ጌታም አለው ሂድ ይህ ለኔ የተመረጠ እቃ ነውና ስሜን ይሸከም ዘንድ በአሕዛብ ፊት በነገሥታትም በእስራኤል ልጆችም ::

አናንያ ንግግሩን እንዲህ ሲል ይቀጥላል የሐዋርያ ስራ ምእራፍ 22 ቁጥር 14ና 15 እሱም ስለአባቶቻችን አምላክ አስቀድሞ መረጠ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድ ጻዲቁንም ታይ ዘንድ ከአፉም ድምጽ ትሰማ ዘንድ በሰው ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንለታለህ ባየኸው በሰማኸው ስራ ሁሉ ።

ጳውሎስ እንዴት እንደተላከ ሲያስረዳ ኢየሱስ እንዲህ ይላል የሐዋርያ ስራ ምእራፍ 26 ቁጥር 16 እስከ 19 ነገር ግን ተነሳና ቁም በእግርህ እኔ ስለዚህ ታየቸሀለሁና እሾምህ ዘንድ እገልጋይ ምስክርም እንድትሆን ባየኸው ነገር በምገልጽልህም ከሕዝብ ሳድንህ ከአሕዛብም ዛሬ ወደሳቸው ከምስድህ ። ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ ከጨለማ ወደ ብርሃን እንዲመለሱ ለሰይጣንም ከመገዛት ወደ እግዚአብሔር የኃጥያታቸውን ስርኤት ይወስዱ ዘንድ እርስትም ከቅዱሳን ጋር በኔ በማመናቸው ። ስዚህ አግሪጳ ንጉሥ ሆይ እመጸኛ አልሆንኩም ከሰማይ ለታየኝ ነገር ።

ግርማዊ ሆይ እኔም እንደ ጳውሎስ ለአደረግሁት የእስልምና ትምህርት ቀንቼ የአፄ ቴወድሮስ መኮንንቶችና የአፄ ዮሐንስ ምስለኔወች እየመጡ ሲያስቸግሩን ያልተመለስኩትን በጌትነቱ የበላይ የለለበት እምላክ ባሳየኝና በገለጸልኝ አመጸኛ አልሆንም ። ሲሉ ንጉሡ ነገሥቱ ለጠየቋቸው በዝርዝር ተንትነው አስረዱ ።

በዚህ አይነት ሁለት ቀን አልፎ ሶስተኛ ቀን ጉባኤው ጉዳዩን በጥንቃቄ ካጠና በኋላ መኳንንቱና ካህናቱ አቡኑና ንጉሡ ነገሥቱ ተመካክረው የማንንም መብት የማይነካ ፍቅርና ሰላምን መተሳሰብንም የሚፈጥር ውሳኔ ጉባኤው ወሰነ ።



## ውሳኔ

ውሳኔውም ሸህ ዘካርያስ በተከሰሰበት ነገር ሁሉ ጥፋተኛ ላለመሆኑ እራሳችሁን እያስነበብንና እያስተረጎምናችሁ በሶስት ጉባኤ ስንመለከተው ምንም ከማስተማር የሚያግደው ከቁርአን ውጭ ያስተማረው የለም ስለዚህ ከሱ የተሻለ ምን መምህር ሊገኝ ነው ከማስተማር ይታገድ የምትሉት ለናንተ ማስተማር ከተፈቀደ ለእርሱ እንዳያስተምር ማገድ መብቱን እንደመንካት ስለሚቆጠር በከሰሳችሁትም ክስ በገዛ ቁርአናችሁ ቃል ስላስረዳ ከማስተማር አይታገድም ሲል ጉባኤው በአንድ ድምጽ ወስኖ ተነሳ ።

# ምእራፍ 15

## አዲስ ከሳሽ

ከዚህ በኋላ ደግሞ ይግባኝ መጠየቅ ባለመቻላቸው ሌላ ዘዴ ፈጥረው ጉባኤው እንደገና እንዲሰበሰብላቸው የወረሂመኑ ፤ የተኩለደሬ ፤ የቃሎ ፤ የወረባቦ ፤ የሰባት ቤት ወሎ እስላሞች ሁሉ ተሰብሰበው መጥተው ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክን ዳኝነት ይሰጡን ፍትህ ርትዕ ያውጡልን እንዴት ሃይማኖትን ያህል ነገር ሳንረታና ሳንከራከር እንተዋለንን ? ካሁን ቀደም የተረቱት ያልተማሩና ኢልም ያላወቁ ናቸው አሁን ግን እውቀት ያላቸውና እርቃን የሚተረጉሙትን አምጥተናል ብለው አመለከቱ ።

በዚህ ምክንያት ጉባኤው አንደገና እንዲሰበሰብ ስለተደረገ እንደፊተኛው ሁሉ ሊቃውንትንና ወንበሮችን መኳንንትና መሳፍንትን ሰብስበው ጉባኤ ተከፍቶ ንጉሠ ነገሥቱ በተገኙበት ክርክር ቀጠለና አቤት ባዩ እንዲህ ሲል አመለከተ ፡፡

ግርማውይ ሆይ በሃይማኖታችን ሥነ ስርአት መጠጥ ሀራም ነው ይላል ዘካርያስ ግን ቢጠጣ ምንም አይደል በማለት ስርአታችንን ያፈርሳል ። ሁለተኛ ሙሐመድ የእሰላም መልክተኛ ነኝ ከኔ በኋላ ሌላ መልክተኛ አይነሳም ያለውን አላህ ሳከኝ እያለ ሕዝቡን ያታላል ከተግባሩ ታግዶ በስርአት አፍራሽነቱ ሊቀጣ ይገባዋል ። በተጨማሪም በሶላት ጊዜ ፊትን ወደመካ ዙሮ አንዲሰገድ የእስልምና ስርአታችን ያዛል ይህንም ዘካርያስ ተቃውሞ ወደፈለገው አቅጣጫ ዞሮ ይሰግዳል በዚህ ሁሉ ትእዛዝ አፍራሽነት ከተግባሩ ታግዶ ሊቀጣ ይገባዋል እሉ ።

ለከሳሾች የተከሳሽ መልስ መጠጥ መብል የግል በመሆኑ ቁርአናችሁ በወንጌል መንገድ ሂዱ ሃይማኖታችሁ ናትና እያለ በገጽ 227 ምእርፍ 21



አል አንቢያ ክፍል 17 ቁጥር 91 እና 92 ተመልክቱ እንዲሁም በገጽ 78 ምእራፍ 5 አል ማኢዳ ቁጥር 1 አላንት የመጽሐፍ ባለቤቶች በወንጌልና በኦሪት ሕግ እስክትሰሩ ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም እያለ ይመሰክራል ይህ ቁርአን የሚመሰክርለት ብሉይና አዲስ ኪዳን ስለመጠጥ እንዲህ ይላል ማንም እይፍረድባችሁ በመብልና በመጠጥ ቆለሳይስ ምእራፍ 2 ቁጥር 16 የመጀመርያው ክፍል ፡፡ ማቴዎስ ምእራፍ 15 ቁጥር 11 ወደ እፍ የሚገባ ሰውን የሚያረክስ አይደለም ክአፍ የሚወጣ ግን ይህ ሰውን ያረክሳል ይላል ፡፡ ስለዚህ በመብልና በመጠጥ ሃይማኖት እይመሠረትም መጠጥን መተውና እለመተው በግል ፈቃድ የሚሰራ ስለሆነ በዚህ ልትጠይቁኝ አይገባም ።

እንዲሁም ከሙሐመድ ሌላ ሌላ መልክተኛ አይነሳም የሚሉት አምላክ ሽህ ሶስት መቶ አመታት ከሙሐመድ ወዲህ የተነሳውን ትውልድ ያላንዳች መምህር ያላንዳች የአምላክ መልክተኛ አስቀመጠው ማለት ነውን ? አይደለም ፡፡ ኤልያስ በዘመኑ እኔ ብቻ ቀረሁ ብሎ ነበር ግን ጌታ የእርሱ የሆኑ ሰባት ሽህ እንደነበሩት ገልጾለታል ፡፡ 1ኛ ነገሥት ምእራፍ 19 ቁጥር 18 እንዲሁም ሙሐመድ ከኔ በኋላ ሌላ የጌታ መልክተኛ አይነሳም ቢልም አምላክ ግን የሚለው እንደሚከተለው ነው ፡፡ ዮኤል ምእራፍ 2 ቁጥር 23ና 28 አላንትም የጽዮን ልጆች በእግዚያብሔር በአምላካችሁ ደስ ይበላችሁ እልልም በሉ ፡፡ ለመጽሂት መምህር የሚሰጣችሁ የፊተኛውን ዝናብ በጊዜው ሰጥቷችኋልና ለናንተም የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ ቀድሞ አንደ ነበር ያወርድላችኋል ፡፡

ከዚህ በኋላ ይሆናል ስጋ በለበሰ ሁሉ መንፈሴን አፈሳለሁ ወንዶች ልጆቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ

ትንቢት ይናገራሉ ሽማግሌዎቻችሁም ህልም ያልማሉ ጎበዞቶቻችሁም ራእይ ያያሉ ይላል ።

በዚህ ተስፋ መሰረት በዚህ ጊዜ ሊጠራኝ መሆኑን እንድትገነዘቡ እወዳለሁ ። እንቀበልም ብትሉ የራሳችሁ ፋንታ ነው ለሚቀበሉኝ እንዳላስተምር ልታገድ አይገባም ።

በሶላት ጊዜ ፊትን ወደ መካ አዙሮ መስገድ የእስልምና ሥርአት ነው ። ይህን ሥርአት አፍርሶ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ሆኖ ይጸልያልና ትእዛዝ አፍራሽ ነው ይቀጣና ከዚህ ተግባር ይታገድ የሚሉት ለምንድነው ጌታን በአንድ አቅጣጫ የሚወስኑት እኔን የፈጠረ አምላክ በሁሉ ለመገኘት እንደሚችል ባለመዝሙሩ ዳዊት በቁርአን ገጽ 195 ምእራፍ 17 አል እስረእ ክፍል 15 አንቀጽ 55 ዳዊትንም መዝሙርን ሰተነዋል ይላል በዚህ በመዝሙሩ ምእራፍ 139 ቁጥር 6 እና 149 እውነትህ ትነግረኛለች ከፍ ከፍም ትልብኛለች እንደርስባትም ዘንድ አይቻለንም ከመንፈስህ ወዴት አከዳለሁ ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ ወደሰማይ ብወጣ አንተ ከዚያ ነህ ምንጣፌንም በሲኦል ባነጥፍ ከዚያም እነሆ አንተ አለህ የወገግታም ክንፎች ብወስድ በባህር ዳርም ብቀመጥ ከዚያ ደግሞ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች በጨለማም ትሰውረኝ ብየ ብል ሌሊት በዙሪያየ ብርሀን ይሆናል በአንተ ዘንድ ጨለማ አይጨልምምና ሌሊቱ እንደ ቀን ያበራል እንደ ጨለማው እንዲሁ ብርሃኑ ነውና ። አንተ ኩላሊትን ፈጥረሀልና በናቴም ሆድ ሰውረኸኛልና አቤቱ ግሩምና ድንቅ ሆኘ ተፈጥርያለሁና አመስግንሀሉሁ ስራህ ድንቅ ናት ነፍሴም እጅግ ታውቃለች ።



ስለዚህ እናንተ ወደ መካ ብቻ ተወስናችሁ ብትለምኑት እኔና እኔን የመሰሉት ግን አምላክን በአንድ አቅጠአጫ ልንወስነው አንችልም ሲሉ መልስ ሰጡ ።

አሁን አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ ላይ አዲስ ክስ የከሰሱት የወሎ ሰዎችም ሆኑ በይግባኝ ከላስታና ከዋግ ከትግሬና ከጎንደር የተጠራቀሙትም ቢሆን የክርክሩ ጉዳይ እንዳላዋጣቸው በተመለከቱ ጊዜ ከመካከላቸው አንዳንዶች እየተነሱ ለዘካርያስና እፍኝ ለማይሞሉ ሰዎች ይህን ያህል ምን ያስጨንቀናል እሱን እንደምንም ብናጠፋው ተከታዮቹ ይበተናሉ ከዚያ በኋላ እናርፋለን ሲሉ በመመካከር እንደሚያሴሩ ጭምጨምታ ይሰማ ጀመር በዚህ ጊዜ ጉዳዩን በጽሞና ለማጥናት ቀጠሮ ተሰጠና ጉባኤው ተነሳ ።

ንጉሠ ነገሥቱም ስለሚሰማው ጭምጭምታ እርግጡን ለመረዳት በልዩ ተመልካች ሲያስመረምሩ ነገሩ እርግጥ ሆኖ ተገኘ ።

ሸህ ዘካርያስም ቀጠሮ ተቀብለው በወጡ ጊዜ ለደጋፊወቻቸው እንዲህ ብለው ተናገሩ ይባላል ። ወንድሞቻችን ዛሬ ሸፈጥናቸው መጠጥ አሁንም ሀራም ሊሆን ይገባል ምክንያቱም ከመጠጥ ወዲያ አንድ ሰው የእግዚያብሔርን ሕግ ሊያስታውስ ስለማይችል ሕግን በመተላለፍ ኃጥያት በቀላሉ መስራት የታመነ ነው ብለው ተናገሩ ይባላል ። ይህ አነጋገር ኃጥያትን በስሙ ኃጥያት ብሎ ለመጥራት የማይፈሩ እሳቸውም ሆኑ ሌላው ሰው ንስህ መግባት አስፈላጊ መሆኑን የሚያምኑ ሰው መሆናቸውን ያሳያል ።

በእርሳቸው ሕይወት ላይ ሴራ መዶለቱን ሰምተው እንዲህ አሉ ወንድሞቻችን ባንረግማቸውም እንኳ እኛን ከችግር እንዲጠብቀን ጌታን ልንለምን ይገባናል ብለው ታላላቆችን ሰብስበው ቃለ እግዚያብሄር ካሰሙ በኋላ ከድንኳናቸው አጠገብ እሳት አስነድደው ማታ ከታላላቆቹ ጋር በሳቱ ዙርያ ተቀምጠው በሚወያዩበት ጊዜ አንድ ታላቅ ዳሞትራ ከራሳቸው ላይ ጉብ አለባቸው እሳቸውም በጃቸው ከራሳቸው አንስተው ወደሚነደው እሳት ወረወሩትና ኩምትር ብሎ እሳት ሲበላው አይተው የሕያው ባርያ ለኛ የታሰበውን ጌታ ለጠላቶቻችን አደረገው አሉ ።

በማግስቱ በነገረ ፈጅነት ለወሎ ሰወች ቁሞ ሥርአት ቢያዘነብልበት ሌላ የሴራ ዱለት ሲተበትብ የነበረው ሰው ሙቶ የቀብር ስነ ሥርአት እንደሚፈጸም በሰሙ ጊዜ አሁንም ለተከታዮቻቸው የሚያስገርም ሌላ ታምር ተፈጸመና ትምህርት አገኙበት ።

ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ሸህ ዘካርያሰን ከቤታቸው አስጠርተው ከቀጠሮ በፊት ለምንድነው እስላሞች ወገኖችህ እንዲህ የሚጠሉህ ብለው ጠየቋቸው።

ሸህ ዘካርያስም የሰጡት መልስ የሚከተለው ነበር ግርማዊ ሆይ በማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ 10 ቁጥር 18 እስከ 22 ወደ አለቆች ወደ ነገሥታትም ይወስዷችኋል ስለኔ ለራሳቸው ምስክር ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ አሳልፈውም በሰጧችሁ ጊዜ አታስቡ እንዴት ወይም ምን እንደምትሆኑ በዚያን ጊዜ ይሰጣችኋልና የምትናገሩት ። አላንት የምትናገሩ አይደላችሁምና ነገር ግን ያባታችሁ መንፈስ ነው የሚናገርላችሁ ። ወንድም ወንድሙን አሳልፎ ለሞት ይሰጣል እባትም ልጁን ።



ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሳሉ ይገድሏቸዋልም ። በሁሉም ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ስለስሜ እስከ ፍጻሜ ግን የታገሰ እርሱ ይድናል ይላል ።

ስለዚህ ስለየሱስ ስም ነው የሚጠሉኝ ግን እኔን ብቻ ሳይሆን ካሁን በፊት የተከተሉት አስራሁለቱ ሐዋርያት መጠላት ብቻ ሳይሆን ከዮሐንስ በቀር ሁሉንም ገድለዋቸዋል ። የሐዋርያት ሞት ወንጀል ስለፈጸሙ አልነበረም ዳሩ ግን የክርስቶስን የወንጌል ብርሃን ለሰው ሁሉ ሲያበሰሩ ኃጥያት መስራት የሚወዱ ሁሉ ጨለማን ተገን አድርገው ወንጀል ሲፈጽሙ የሐዋርያት ሕይወት በወንጌል ሲያበራ የጨለማን ተገን ሲለሚያስወግድና ጉዳቸውን ስለሚያሳይባቸው በዚህ ተናደው የሚሰነዝሩት ክንዳቸው ለተቀደሰው የሐዋርያት ሕይወት መጥፊያ ምክንያት ይህ ነው ። እኔም የተጠላሁት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ መልክተኛ በመሆኔ ነው ። ሲሉ በትህትና አክብሮት በተመላበት ሁኔታ መልሰ ሰጡ ።ንጉሠ ነገሥቱም ይህ ከሆነ ምክንያቱ ጉዳይህን በተሎ ፈጽመን እናሰነብትህለን አሏቸውና ተሰናብተው ወጡ ።

## 2ኛ ምሳሌ

በማግሰቱ ንጉሠ ነገሥቱ በተገኙበት ሁለተኛ ቀን ጉባኤ ተከፈተና አቡንና ካህናትን መሳፍንትንና መኳንንትን እያሌ አዋቂ ሰወች ተሰብስበው የንጉሠ ነገሥቱ ወንበሮችና አፈ ንጉሥ የሆኑ ሁሉ እየተቹበት ለፍርድ ውሳኔ በቀረበ ጊዜ ሸህ ዘካርያስም ሆኑ ከሳሾቻቸው ምን ይወሰን ይሆን እያሉ ከተጨነቁ በኋላ ከሳሾች የሰጠው መልስ ትክክል ሰላልሆነ ከተግባሩ ታግዶ እስካሁን በሰራው ቅጣት ይገባዋል እያሉ እመለከቱ ። ሸህ ዘካርያሰም ደግሞ እንዲህ ብለው ከፍርድ በፊት አሰሙ ፡፡

ሚስጥር ተገልጸለት በመንፈስ ቅዱስ ፤
ለተበደለ ሰው የልብ የሚያደርስ ፤
ምንይልክ እግዚያብሔር ካንት ወዲያ ንጉሥ ፡፡
አምላክ ከዚህ ሌላ ምን ይልክልሃል ፤
ከፊትህ ላይ ቆሞ ያመለክትሃል ፤
እውነትን ከሀሰት ለይቶ ነግሮሃል ፤
ብይን ለመበየን ስልጣን ተሰቶሃል ፡፡
ከሰማይ በመስኮት ይመለክትሃል ፤
በአእምሮህ መላእከት ድጋፍ ይሰጡሃል፤
ቅን ፍርድ እንድትሰጥ ይጠባበቁሃል ፤
ልበ ቅን ስለሆንህ እምላክ ይወድሃል ፤
የምትፈርደውን እሱ ይነግርሃል ፤
ስለዚህ በስማይ ዋጋ ይቆይሃል ፤
እስከዚያውም ታሪክ ያመሰግኑሃል ፡፡

ሲሉ ተናገሩና ውሳኔው በአዋጅ እንዲሆን ጉባኤው ተሰማምቶ ሸህ ዘካርያስ ለመምህርነት የበቃ የነቃ የተማረ የተመራመረ መሆኑን ጉባኤው ሰላመነበት በተከሰሰው ጉዳይ ሁሉ ፈጽሞ ስለረታ የተከሰሰበት ሁሉ ፈጽሞ ውድቅ ሆኖ ለማስተማር እንዳይከለከል ጉባኤው ወስኖ አሰናበታቸው ፡፡



በዚህ ጊዜ ሸህ ዘካርያስ ከአደባባይ ሲወጡ ደጋፊወቻቸው ሴረኞቹ እንዳይገሉባቸው በሰላሳ ጠብመንጃ ክስባ በማያንስ ጀሌወች በጠቅላላ ወደመቶ የሚሆኑ ሰዎች ክብብ እድርገው ይዘዋቸው ወደ ስፈራቸው ሲጓዙ ንጉሠ ነገሥቱ ከአደባባይ እንደሆኑ በእጉሊ መነጸራቸው ተመልክተው በሰተኋላ እንድ ፈረሰኛ ላኩባቸው ። ተመልሰው መጡና ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቆሙ ። ንጉሠ ነገሥቱም እነዚህ እንተን የሚያጅቡህን ሕዝቦች እንተ ነህ የምታስተዳድራቸው ? እሏቸው ፡፡

ግርማዊይ ሆይ እኔ አላስተዳድራቸውም በበቅሎቻቸው ጫንቃና በበሮቻቸው እንገት ይተዳደራሉ እንጅ ። አሁን እኔን ተከትለው የመጡት ብቻውን ሲሄድ ወንድማችን እንዳይሞትብን ብለው በግል ፈቃዳቸው እኔን ለመጠበቅ የመጡ ወንድሞቸ ለኔ መተዳደሪያ እንኳ እያዋጡ በሚሰጡኝ ድጋፍ ነው ምግባሬን የማከናውን ብለው መለሱ ፡፡

ንጉሠ ነገሥቱም እነዚህ አንተን ለመጠበቅ የደከሙትን ወንድሞችህን ሁሉ ለሁል ጊዜው እንተን ለመጠበቅ ሲከተሉ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ሊገብሩት የሚገባቸው የበሮቻቸው አስራትና የበቅሎቻቸው ቀረጥ ለቀለብ ደመወዝ እንዲሆናቸው ፈቅደንላቸዋል ። ለዚህ ፈቃድ ይሰጣቸው ፡፡ እንዲሁም በባዶ እጃቸው የሚከተሉህ መሳሪያ እንዲኖራቸው እንድ መቶ ከሃያ ናስ ማስር ውጅግራ ተፈቅዶልሀልና ግምጃ ቤት ሄደህ እንድትረከብ ። በራሳቸው መሳርያ የሚያገለግሉህ እኛም በስጠንህ መሳርያ እንተን የሚጠብቁ ሁሉ ከግብር ነጻ ብለናቸዋል ፡፡ ነገ ሸክላ ቤት ገብተህ የአለቅነትህ ማእረግ ስለሚሰጥህ ተዘጋጅተህ እንድትመጣ ፡፡ በተጨማሪም ከእንግዲህ ወዲህ ላንተ

መተዳደሪያ ባመት አራት ሽህ ብር ወስነንልሀል ግምጃ ቤት ሄደህ በተመቸህ ጊዜ እንድትቀበል ። ለባለመሳሪያወችም ስድስት ሽህ ጥይት አዘንላቸዋል አብረው እንዲረከቡ ። ሲሉ ንጉሠ ነገሥቱ አዘዙ ።

በዚህ ጊዜ እጅ ነስተው የተደረገላቸውን ከተቀበሉ በኋላ ተመልሰው ወደ ሰፈራቸው ሲጓዙ ደጋፊወቻቸው ሁሉ በደስታ እየፈነደቁ ለነገው የቀሚስ ሽልማት በመዘጋጀት አደሩ ። እንቅልፍም ሳይወስዳቸው በእግዚአብሔርና በባላደራው ንጉሠ ነገሥት ምስጋና ሌሊቱን እነጉ ። ሲነጋ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አደባባይ ሲደርሱ የንጉሥ ቃል እንድ ይበቃል እንደሚባለው ሁሉ እረጅም ዋርዶ ስናር በቅሎ በወርቅ መረሻት የተንቆጠቆጠች ያጌጠችበት መሳርያ ለአይን የሚያንጸባርቅ ኀበዛዝት ይዘዋት ስድስት ሴቶች ምግብ በማዘጋጀት የሰለጠኑ ስራ አዋቂወች ከሙሉ ድርጅት ጋራ አብረው ቁመው ንጉሠ ነገሥቱ ካሉበት ሸክላ ቤት እልፍኝ እስከልካዩ ይዟቸው ገባ በወርቅ የተንቆጠቆጠው ካባ ከላያቸው ተደረበባቸውና ከእንግዱህ ወዲያ በወደድከው አገር እየተዘዋወርህ እንድታስተምር ፈቅደንልሀል ። አንተ የክርስቶስ ገንዘብ ስለሆንህ ስምህ ከዛሬ ጀምሮ አለቃ ንዋየክርስቶስ ተብለህ ትጠራለህ ። እኛ ከወሰንልህ መተዳደሪያ ሌላ አስራቱን ፍየል ምልምሉን እና ግብሩን በጠቅላላ የእተቀበልህ የምትተዳደርበት ሶስት ደብር አገር ፈቅደንልሀል የምትመርጣቸውን በጽሁፍ ግለጽልን ተብሎ ክንጉሠ ነገሥቱ እንደበት ተነገራቸው ። ቁመው በሰልፍ የተቀበሉትን መቶ ህያ ጠብምንጃ ታጅበውበት ለመጀመርያ ጊዜ ከመውጣታቸው በፊት ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲህ ብለዋል " መንግስተ ሰማይን ከሞት ወዲያ ማዶ ነበር እንጅ በምድር ላይ እልተጠባበቅሁም ነበር አሁን ግን ጻዲቁ ንጉሥ ሳደረጉልኝ ወሰን የሌለው ክብር አምላክ



በምድር እንዳነገሡዎት የሰማይን መንግሥት ያውርስልኝ ። ሲሉ ከመረቁ በኋላ ፊታቸውን መለስ ሲያደርጉ አቡነ ማቴዎስ ደግሞ ስልሳ መጽሐፍ ቅዱስ አምጥተው በአማርኛ የተጻፈ በል እንካ በዚህ አስተምርበት አሏቸው ። ይህን ሁሉ ሽልማት ተሸልመው አለቃ ንዋየክርስቶስ ወደ ሰፈራቸው ሲጓዙ በጊዜው የነበሩት እምቢልታ መለከት ነጋሪት እየተብላላ ከሰፈራቸው ዋርዲት ላይ ተቀምጠው በደረሱ ጊዜ የነበረውን ደስታ ማንም ሊገምተው ይችላል ።

*ሸህ ዘካርያስ ከእስላሞች ጋር በተከሰሰበት ነገር ሁሉ በቁርአን እረትቷል ስለዚህ ከአሁን ቀደም በቁርአን ቃል የሚተዳደረውን እስላም ሁሉ በወደደው አገር እየሄደ እንዲያስተምር ፈቅደንለታል አሁንም ከዛሬ ጀምሮ ሸህ ዘካርያስን ወይንም ደረሶቹን በሱም ትምህርት የረጉትን ሰወች ማንም በሀይማኖት የተነሳ አውካለሁ ቢል ሁለተኛ አይከሰሱ ። ሸህ ዘካርያስ በተከሰሰበት ነገር ሁሉ ፈጽሞ እረቷልና የዚህ የአዋጅ ቅጅ በሸህ ዘከርያና በደረሶቹ እጅ በቤተ መንግስትም ይቀመጣል ለዘላለም ምስክር ይሆን ዘንድ እኛም ይህን አዋጅ ማስነገራችን እስላም ለእስላም ሁለተኛ እንዳይጣላ ብለን ነው ። ግንቦት 5 ቀን 1899 ዓ.ም አዲስ አበባ ተጻፈ ። "*

*================*

የሚል የአዋጅ ቃል ተጽፎ ከመቶ በላይ ተራብቶ በማግስቱ አዋጅ ዲዝ ዲዝ እየተደረገ ነጋሪት ከተመታ በኋላ ሕዝቡ ሲሰበሰብ ስማ ብሰውሀል መስሚያ አይንሳህ እያሉ ከአዋጅ በኋላ ከዚህ በላይ ተጽፎ የቆየው የአዋጅ ቃል ተነበበና የተጻፈው የአዋጅ ቃል ለአለቃ ንዋየክርስቶስና ደጋፊወች ታደለ ።



## *ምእራፍ 17*

## *የመልስ ጉዞ*

ሕዝቡም የአዋጁን ቃል ሰምቶ ሲመለስ አለቃ ንዋየክርስቶስ የአዋጁን ቃል ተቀብለው ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ ። ከዚህ በኋላ አለቃ ንዋየክርስቶስ ደጋፊዎቻቸውንና ተከታዮቻቸውን ሰብስበው ከቤታችን ስንወጣ እንዲህ ያለ እድል እንደሚገጥመን ባንጠረጥርም ሰማይ ምድርን የዘረጋ ባህሩንና ደረቁን የፈጠረ አምላክ በንጉሠ ነገሥቱ በመንፈሱ አድሮ ጸጋ ሞገሱን አጎናጸፈን ። በሰፊ ችሮታ ለተቀበሉን ንጉሠ ነገሥት ባለውለታ ስለሆን ከዛሬ ጀምረን ከልብ ለንጉሠ ነገሥቱና ላገራችን በታማኝነት ማገልገል ይገባናል ። ብዙ የተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታል እንደተባለው ሁሉ ግርማዊነታቸው ያደረጉልን ስጦታ ከአሁን ቀደም ለፈጸምነው ነገር ብቻ ሳይሆን እንግዲህም በተግባራችን ትጉህ መሆን ይፈለግብናል ብለው ከተናገሩ በኋላ ለኔ አዲስ ሰም መቀበሌን ሰምታችኋል ከናንተ መካከልም አዲስ ስም የምሰጠው አለኝ ብለው ከአድዋ የተከተላቸውን አህመዲንን ተክለሃይማኖት ብለው ሰየሙት ፤ መሐመድ አማኜን አለቃ ቦጋለ ብለው ሰየሙ ጠቋሬን ባሻ ብለው የብረቱ ሁሉ አለቃ አድርገው ሾሟቸው ። በዚህ አይነት እየተደሰቱ ነገሩ ካበቃ በኋላ ለአንድ ወር ያህል አዲስ አበባ ቆይተው ተከታዮቻቸውን ሁሉ ብዙዎቹ ቁርአኑን በአረብኛ ብቻ ነበር የሚያነቡት በዚህ ጊዜ ግን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ 60 የሚሆን አቡነ ማቴዎስ ስለሰጧቸው በተጨማሪም ለያንዳንዱ ተከታያቸው የሚበቃ ገዝተው ጨምረው አለቃ ንዋየክርስቶስ ተከታዮቻቸውን ሁሉ ትልቅ ትንሽ ሳይቀር ያማርኛ ፊደል ገዝቶ እንዲማርና መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ የተጻፈውን እራሱ እንዲያነብ ስለመከሯቸው ሁሉም በደስታ ስሜት መማር ስለጀመሩ ልዩ ስጦታ ያላቸው አዲስ አበባን ሳይለቁ ማንበብ ጀምረው ተገኙ ። በዚህ አይነት ከተዘጋጁ በኋላ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው በደስታ በ150

ብረት ታጅበው በሰላም ተጉዘው ደብረታቦር ደረሱ ።

ደብረታቦር በደረሱ ጊዜ አስቀድሞ ሰው ተልኮ ስለነበር ድግስ ተደግሶ ሕዝቡ ከትግሬ ፣ ከዋግ፣ ከላስታ፣ ከወልቃይት፣ ከበለሳ፣ ከጎንደር፣ ከጋይንት፣ ከፋርጣና ከእብናት መጥቶ የደብረታቦርን ከተማ ሰፍሮበት ሲጠባበቅ በወርቅ መርሻት በጠለሞች በቅሎ ላይ ተቀምጠው በወርቅ የተንቆጠቆጠውን ካባ ደርበው በ150 ብረት ታጅበው የጠብ መንጃው መሳርያ ወርቅ የመሰለ የናስ ማስርያ ያለው በመሆኑ በየጠብመንጃው ክሁለት ላይ የወርቅ አምባር እንዳጠለቀች ሴት ሲብለቀለቅ ጊዜ 120 ጠብመንጃ የዚህ አይነት ስለነበረ በዚህ ቀን ተገኝተው ሰልፉን የተመለከቱ ግሩም ትንግርት በማለት እግዚያብሔርንና ንጉሠ ነገሥቱን አፄ ምኒልክን አመሰገኑ ። የወንድማቸው ሚስትም ወይዘሮ ምጥን እሁንም እንዲህ ሲሉ ገጠሙላቸው -

እናስቆርጣለን እናስፈልጣለን ብላችሁ ሂዳችሁ፣
በመቶ እምሳ ብረት ታጥሮ መጣላችሁ ።
ምናሌ ልጅዎ አማረች ሚስተዎ፣
ከላይ ከንጉሡ ብናስተያየዎ፣
አምላክን ሊያክሉ ምንም አልቀረዎ ።
ጠላቶቹ ሁሉ ቢገፉ ቢገፉ፣
ዞዛንባር ተራራ አርገውት እረፉ ።
የአጀቡሽን አባት ዝናብን መታው፣
እኔ እጎዳ እንደሆን ክፍ ከፍ ያድርገው፣
ኧረ እናንተ ሰዎች ነገሩ እንግዳ ነው፣
በእውነት ከልብ አምላክን ላመነው፣
የሚሰራው ስራ እንደዚህ እንጅ ነው፣
እሁን ከዚህ ቁሜ ስንቱን ልናገረው፣
ለሚመጣው ትውልድ ታሪክ ይመስክረው ።
ትግሬ ላይ እንዲያ ቁመው ሲሟገቱ፣



ፋርጣ ላይም እንዲያ ሲያደቡ ሊማቱ፣
ሸዋ ላይም እንዲያ ሲለፉ ሲታክቱ፣
ምን አስከሰሳቸው እንደዚህ ሊረቱ፣
ውሸት መች ይቆማል ሲመጣ እውነቱ፣
ሁሉ ተገለጠ እስከመስረቱ፣
የሰው ሁሉ ሱሪ እስከቁርጭምጭምቱ፣
ንዋየክርስቶስ ተባቱ ተባቱ ።

ሲሉ ገጠሙላቸው ። አለቃ ንዋየክርስቶስም እግዚያብሔርን አመስግነው ክርስትና ከመነሳታቸው በፊት እንደገና የሐዋርያነት ተግባራቸውን በትጋት ሲያከናውኑ ምንም እንኳ የጽሁፍ መሳርያ እንደልባቸው ባያገኙና በአማርኛ እራሳቸው ለመጻፍ ባይችሉም በአረብኛ የጻፉትን አለቃ ኢሳያስ ወንድምእገኘሁ ወደ እማርኛ በቁም ጽሁፍ እየተረጉሙላቸው ያስተምሩ ነበር ።

## *ምእራፍ 18*

## *የአለቃ ንዋየክርስቶስ መጠመቅ*

አለቃ ንዋየክርስቶስ እግዚያብሔር በራእይ ተገልጦ የሰጣቸውን መልእክት በኃጢአትዋ ወደ ጥፋት የተቃረበችውን ዓለም ማስጠንቀቂያ እንዲሆን እግዚያብሔር አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን ቆይቶም በአዲስ ኪዳን የተገለጠውን መልእክት በቁርአን ከመረዳታቸውም በቀር ቁርአን ወደ ብሉይና አዲስ ኪዳን ስላመለከታቸው የቁርአን ቃል ከብሉይ ከአዲስ እያመሳከሩ በማስተማራቸው ወሎ ከዋግ ሹም ጓንጉል ላይ፣ ትግሬ ከደጃዝማች ገብረስላሴ ላይ፣ በጌምድር ከራስ ጉግሳ ላይ እየተከሰሱ በረቱ በይግባኝ አዲስ አበባ ላይ አጠቃለው ስለረቱ ሊቅነታቸውን ከንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ፊት ስላስመሰከሩ እንዲያስተምሩ በአዋጅ ስለተፈቀደላቸው ከክርክር በፊት እስከ 1899 ግንቦት 5 ቀን ድረስ 15 ዓመታት ከክርክር በኋላ እስከ 1903 ዓ.ም ድረስ አራት አመት በጠቅላላ 19 ዓመት በእስልምናቸው እንዳሉ ከአስተማሩ በኋላ ስርአተ ጥምቀትን 1903 ዓ.ም ደብረታቦር ላይ ንጉሥ ወልደ ጊወርጊስ በተገኙበት በአባ ሃናንያ እጅ ስርአተ ክርስትናን በጥምቀት ተቀበሉ ። የእሳቸውን መጠመቅ በያለበት በሰማ ጊዜ ትምህርቱን በሳቸው ተቀብሎ የሳቸውን መጠመቅ ሲጠባበቅ የቆየው ሁሉ ስለተጠመቀ በዚያን አመት የተጠመቀው ሕዝብ ቁጥር ከሶስት ሽህ በላይ እንደነበር ይነገርለታል። የአለቃ ንዋየክርስቶስን ጥምቀት ምክንያት በማድረግ በጎንደሩ ሊቅ አለቃ ታየ የተባሉት ከስፍራው በመገኘት ስለአለቃ ንዋየክርስቶስ በእምላክ መጠራትና ስለአከናወኑት የሐዋርያነት ተግባር የሚከተሉትን በጽሁፍ አቅርበዋል ።

አለቃ ታየ ስለ አለቃ ንዋየክርስቶስ በግጥም መልክ ያቀረቡላቸው ጽሁፍ !



### *'ስለ ንዋየክርስቶስና ከሳቸው ጋር ስለተጠመቁት እስላሞች'*

1. እስላም በሙሐመድ በቁርአን የሚያምን ፤
 ክርስትና አንገባም እንተውም ቁርአንን ፤
 ብሎ አሸንፏቸው አፄ ቴወድሮስን ፤
 አፄ ዮሐንስም በኃይል በስልጣን ፤
 አጥምቀውት ነበር የግድ እስላሙን ፤
 ደግሞም አስቀበሉት ስጋወደሙን ፤
 ተምሮ ሳያምን ሳያውቅ ሚስጥሩን ፤
 የግድ ነበርና ያረጉት ይህን ፤
 እጅግ ተቀሰለ ሆነ ምናምን ፤
 አጥብቆ አረከሰው ጸጋ ጥምቀትን ፤
 እንዲህ ሲል አፌዘ በክርስትያን ፤
 ምንድነው በጥምቀት የሆነው አሁን ፤
 ውሃውንማ እኛ እልቅ እንወደዋለን ።
 ጥዋት ማታ ሁለጊዜ መታጠብ ገላን ፤
 ቁርባን በሚሉትስ ምንድን አገኘን ፤
 ስንዴን ዳቦ ወትሮ እንበላው የለን ፤
 ከቶም እስክንጠግብ እስኪሰለቸን ፤
 ምን እንዳትጎዳን ጉርሻ የማትሆን ፤
 ይህንን እያለ እስላም ሲንቀን ፤
 መሳለቅ አበዛ በቅዱስ ቁርባን ፤
 እስላሙም አልተወ የጥንት ያባቱን ።

2. አምላክ ይህን ሰምቶ አመጣ ማቱን ፤
 በክርስቲያን ላይ በሽታ እራብን ፤
 ስጋዎ ደሙ ቢረክስ በምድረ ካህን ፤
 በስላም እጅ ጣላቸው ካህን ንጉሡን ፤
 አረደው ማረከው ድርቡሽ አበሻን ፤
 ደግሞ አበረታበት እሰበሱ ጦርን ፤
 ይገድለዋል ሆነ ወንድም ወንድሙን ፤
 እየቀማ ፈጀው ኃያል ደካማን ፤
 እንደ አስተባላ ታላቅ ታናሹን ፤

16. ከገሀነም ዳነ ነብሱን ከሚገድል ፤
እጥብቆ ከሚያምነው እግዚያብሔር ልዑል ፤
ወደ ልጁ መራው ወደ አማኑኤል ፤
በወንጌሉ መብራት በመንፈሱ ኃይል ፤
አምላክ ይቅር አለው ሁሉን የሚችል ፤
እለቃ እደረገው የአዲሱቹ አምበል ፤
በሃይማኖት ጸና ያለ ውልውል ፤
ተጠምቆ በረታ በክርስቶስ ቃል ፤
ገሀነም ሳይነካው ሳያየው ሲኦል ፤
ከወገኑ ጋራ በማይታበል ፤
በዘላለም መንግሥት በጽድቅ ይኖራል ፤
በተጠመቀበት ቀኑ ቢውል ፤
በታላቅ ጉባኤ በስርዓት በውል ፤
ለሱ መታሰቢያ አርጉለት ብዓል ።

17. ብዓል አድርጉለት በታላቅ ጉባኤ ፤
በወሩም ባመቱም ደግሞም በሱባኤ ፤
መታሰቢያ እንዲሆን በእለተ ትንሳኤ ፤

18. ንዋየክርስቶስ ያላቀው እግዜር ፤
ዋርዳ ከወፍ ልዩ ላባዋ እንደ ሀር ፤
እሱም እንዲሁ ነው ልዩ በነገር ፤
ክርስቶስ ቢመርጠው በታላቅ ሚስጥር ፤
ርህሩህ ነውና ቸሩ አምላክ ክቡር ፤
ስሙን አስታወቀው ከዳር እስከዳር ፤
ቶማስ እንደሄደ በሕንዶች ምድር ፤
ስሙ ተሻገረ ከዳር እስከ ባህር ።

19. የአምላክ ጥበብ አይመረመርም ፤
መደነቅ አናብዛ እንበለው ግሩም ፤
ረዲኤቱ ታላቅ የመድኃኒያለም ፤
ጠቢብ ከሱ ሌላ በዚህ እለም የለም ፤
ህሊናን መርማሪ ኃይሉ የማይደክም ።



20. ጌታ ቢፈቅድለት ንዋየክርስቶስ ፤
ታላቅ ጸጋ አገኘ በጥምቀት መታደስ ፤
እግዚያብሔር ቢመርጠው በክፉ ሀሳቡ ባይረክስ ፤
ነገሩን አጸና በወንጌል ቃል ቅዱስ ፤
ሆዱም አልሻከረ ከቁርአን ሲመለስ ።

21. ጻድቃንም ደስ አላቸው አምላክን ባረኩ ፤
ፍጥረቱን ለሚምር እሱን ለሚያመልኩ ፤
ሁሉን ለሚያኖረው በስርዓት በልኩ ፤
አምላክ እንዲህ ይላል ወንጌልን አትንኩ ፤
ሕይወትን አትርሱ በከንቱ አትመኩ ።

22. የአምላክን ጥበብ እዩ ብልሀቱን ፤
ክብሩን ገለጠለት ለሰላም ወንጌልን ፤
ብዙ ያስደንቃል ለስማ ይህን ፤
ሩህሩህ ነውና ሰጠ ምህረቱን ፤
ሰላም ለእስላም ወገን ሆነ ክርስትያን ፤
ላምላካችን ክብር ምስጋና ይሁን ፤
ምእምናን ብዙ የካዱ ቁርአን ፤
ታላቅ ጸጋ አገኙ የሰማይ ቤትን ።

23. እግዚያብሔር ይመስገን የከበረው ልዑሉ ፤
አምላክን አመኑ እሱን ተከተሉ ፤
ለሁሉ ይበቃል የከበረው ቃሉ ፤
ቃሉን ተቀበሉ ክቶ ችላ አትበሉ ፤
ታላቅ ነው ምህረቱ ይረዳል በኃይሉ ፤
የከበረ ጸጋው አለ በወንጌሉ ፤
በቁርአን ትምህርት እንዳይታለሉ ፤
ፍዳን ተሳፈሩ እስላሞች ተጣሉ ።

24. መሬታ የለለው ንዋይክርስቶስ ፤
እርኩስ ነገርን አረገው ፍርስርስ ፤

24. በወንጌል ቃል አምኖ ልቡን እንዲቀድስ ፤
ደረሰው ሁሉ ስራው በመታደስ ፤
እርስቱን ለይቶ ቅዱሱን ከእርኩስ ፤
ታላቅ አባት ሆነ የአዲስ ሕዝብ አራስ ።

እንደ የሱብ ክርስቶስ በጥምቀት ስርአተ ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ አለቃ ነዋየ ክርስቶስ የእግዚያብሔር ልጅነትና የክርስቶስን ወንድምነት ብቻቸውን ሳይሆን በሶስት ሽህ የሚቆጠሩ ወንድሞችና እህቶች አስከትለው የሰማይና የምድር ፈጣሪ የልዑል እግዚያብሔር የቤተሰብ አባል ለመሆን በጥምቀት በራፍ ወደ ክርስትያን በመግባት ተደባለቁ ። ለሀያ አመታት ሊመጡልን ነው እያሉ ሲጓጉ የነበሩት ክርስቲያኖችና ባለስልጣኖች ከጊዜው መርዘም የተነሳ ህልም ሆኖ ሲቀር ይሆን ይባል የነበረ ፍራቻ ተወግዶ ይህ የመንፈስ አንድነት ስለተመሠረተ በጠብ ስፍራ ፍቅር ነገሰ ። በመለያየት ፈንታ አንድነት ሰፈነ ። በበጌምድር በጎንደር በላስታና በዋግ በወሎ በትግሬ ታላቅ ደስታ ሆነ ።

የሰማይ አምላክ በፈቃዱ እጁን የሰደደበት ይህ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ታላቅ ድጋፍን አስከትሎላታል ። አስቀድሞም በሃይማኖት እየተጠጉ አገር ለማቅናት የተሰለፉትን ቱርኮችና ምስራውያን የክርስትያን ደሴት የምትባለውን ኢትዮጵያን አይናቸውን ስለጣሉባት ከጦር ስራዊታቸው ይልቅ ሃይማኖታቸውን የበለጠ መሳርያ አድርገው ለመጠቀም የሃይማኖት መሰላቸውን ለማታለል እና ሀገሩን ከድቶ እነሱን እንዲደግፍ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል ። በዝች አለማችን ላይ እንኳን ሃይማኖት አገርህን ስጠኝ ማለቱ የተለመደ ዘዴ ነው ። ዳሩ ግን ብልህ የኢትዮጵያ ሕዝብና መሪወቹ የፖለቲካውን በፖለቲካ የኃይሉን በኃይል ሲመልሱት መኖራቸው የታመነ ነው ።



<u>ለምሳሌ</u> ፡ አፄ ቴወድሮስ እየደጋገሙ በመተማ በኩል የሚያስቸግሯቸውን መልሰው ነበር ። እንዲሁም አፄ ዮሐንስ በምጽዋና በመተማ እየተነሱ የሚያስቸግራቸውን ኃይል ለመቀነስ በግድ ክርስትና ማንሳት ጀምረው ደከመውበት ነበር ። ጉዳዩ በርትቶ የከበረውንና ላገራቸው ሊሰውላት የሚችሉትን የመጨረሻ ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ደህንነት አበረከቱላት ። አምላክ ይህን ልግስና ተመልክቶ ለኢትዮጵያ ደህንነት ለክርስትና እምነት ዋስትና የሚገኝበትን ለኢትዮጵያውያን ለማስጨበጥ ብሎ በሃይማኖት እያታለሉ አገራቸውን ለመንጠቅ እንደመሳርያ የሚጠቀሙባቸውን ህዝቦች ስህተታቸውን ለማሳየት ከመካከላቸው ከሃይማኖት መስሎቻቸው ለአንዱ በመገለጡ እንደምን እንደተገለጠላቸው ባለፈው ገልጨዋለሁ ። ይህ አምላካዊ ራእይ ለነብስ ጉዳይ መፍትሄ ከመሆኑ በቀር በውስጥ አስተዳደር አንድነትን በመመሥረቱ በውጭ የሚመጡትን እንቅፋት ስላገዳቸው ለሀገሪቱ እድገት ታላቅ ድጋፍን መስጠቱ የማይካድ መፍትሄ ሆኖ ተገኝቷል ።

አለቃ ንዋየክርስቶስ እንደ ኃዋርያት አስቀድሞ በቤት ቀጥለው በጎረቤት ከዛም ባደባባይ የተሰጡትን መንፈሳዊ ስጦታ በታማኝነት ለሕዝቡ በማስተላለፍ ግዳጃቸውን በመፈጸማቸው በትግሬ በዋግና በበጌምድር እየተካሰሱ እውነትን ክህሰት አበጥሮ እንጠርጥሮ በመለየት ላለመግባባት እና ለግጭቱ ሁሉ መፍትሄውን በማግኘታቸው የማያውቃቸው እንዲያውቃቸው እሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሳቸውን አምላክ በአደባባዩ ለሕዝብ በማስተዋወቃቸው እንኳ በገጽ ያዩዋቸውንና የሚያውቃቸውን መኳንንትና ባለስልጣኖች ይቅርና ያላዩዋቸውን ባለስልጣኖች እራሳቸውን በማግኘት ለመተዋወቅ ጉጉት ያድርባቸው ጀመር በዚህ ምክንያት

ዝናቸው ከሰፈር ወዳገር እስከ ንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን በለደረሰ ወዲያው እንዲቀርቡ ተደርጎ ከንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን በቀረቡ ጊዜ የቀረበባቸውን ክስ በመንፈስ ቅዱስ በሚመራ አእምሮ መለኮታዊ ለዛ በተዋሀደው አንደበት ጸጋ የተሞላ ምላሽ በመስጠታቸው የቀረበባቸውን ክስ ውድቅ ከማድረጋቸው በቀር በንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ዘንድ አለቃንዋየ ክርስቶስ ማን መሆናቸውን አስመሰከሩ ንጉሠ ነገሥቱም ሁኔታውን በሚያጠኑበት ጊዜ በኒሁ የእግዚያብሔር ሰው በአለቃ ንዋየክርስቶስ በዛው ጉዳይ ሌሎች ሰዎች ቢከሷቸው በአንድ ጉዳይ ሁለተኛ እንዲከሰሱ ፈቅደው ጉዳዩን በሰፊው በጥንቃቄ ሲያጠኑት አሁንም አለቃ ንዋየክርበቶስ ፍጹም ከላይ ከመለኮት የተላኩ የእግዚያብሔር ሰው መሆናቸውን በሰፊው ተገነዘቡት ።

በዚህ ጊዜ በልዑል እግዚያብሔር ተልኮ የመጣባቸውን እንግዳ አምላክ በሚቀበለው መንገድ አስተናግደው ሹመው ሸልመው አክብረው አስከብረው በሕዝብ ፊት አስደስተው በተግባራቸው የሚደግፍ የአዋጅ ቃል በማህተማቸው አጽድቀው የባላንበሳ ማህተም በሳቸውና በተከታዮቻቸው እጅ አስጨብጠው አሰናበቷቸው ።

አለቃ ንዋየክርስቶስ በቀኝ መንገድ ተመልሰው ከትውልድ ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ በተሰማሩበት ተግባር አራት አመታት ያሀል ከክርስትና በፊት ብሉይ ከሀዲስ እና ከቁርአን እያነጻጸሩ ያላንዳች ቸልተኝነት ካስተማሩ በኋላ አባቸው በተጠመቁ ጊዜ ተማሪወቻቸው ሁሉ ምሳሌያቸውን ተከትለው በመጠመቃቸው ለወገኖቻቸው ለደጋፊወቻቸው ለባለስልጣናት ሁሉ ደስታና ፍቅር ሰላም የሰፈነበት ምክንያቱ ይህ ነበር ።



ንጉሥ ወልደ ጊወርጊስ አለቃ ንዋየክርስቶስ በተጠመቁ ጊዜ የደስታው ተካፋይ ሁነው ለአዲሶቹ ክርስቲያኖች ሙሉ ግብር በማግባታቸው በሃይማኖት ምክንያት በአንድ ካራ እንዳይበሉ ወንድማማቹን ሕዝብ አለያይቶ የነበረውን የእውቀት ጉድለት በመለኮታዊ ራእይ ድጋፍና በአለቃ ንዋየክርስቶስ ትጋትና ታማኝነት ለመምህርነት መለኮታዊ ራእይ ለመቀበል ብቁ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት መለያየት ተደምስሶ መገናኘቅና አንድነት በመመስረቱ በሶስት ሽህ የሚቆጠረው ሕዝብ በአንድ ሌማት በመብላቱ ስህገሩ ችግርም ሆነ ደስታ በወንድማማች መንፈስ እንዲቀበለው በአንድ የፍቅር ማሰሪያ አስተሳሰረው ። ከዚህም ቀጥለው ቀስ በቀስ ከአስር ሽህ የሚበልጡ እስላሞች በያውራጃው በለተጠመቁ የአንድነቱ መንፈስ እያደር ይጎለምስ ጀመር በመብል በመጠጥ ብቻ ሳይሆን በጋብቻም ጥንተ ክርበቲያንና አዲስ ክርስቲያኖች ያላቸው አንድነት በመንፈስና በእምነት ብቻ ሳይሆን በአካልም የተዋሀደ የተዛመደ መሆኑ እያደር እየጎለመሰ ሄደ ።

ንጉሥ ወልደጊወርጊስ ወደ ትግሬ በዘመቱ ጊዜ አለቃ ንዋየክርስቶስ ከንጉሡ ጋር አብረው በመዝመት ከደብረታቦር ተነስተው በደንቀዝ አድርገው ወገራን አድርገው ይጓዙ ጀመር ። በየደረሱበት ከማስተማራቸው በቀር በድሮ ጊዜ እያሌ ሰራዊት የንጉሡን ጉዞ ሲያጅብ አስፈላጊ ስለነበር የአለቃ ንዋየክርስቶስ ደጋፊወች 150 የጦር መሳርያ የያዙ ሲከተሉዋቸው እያሌ ሊቃውንትና መምህራን እንዲሁም ተማሪወች አብረው ስለዘመቱ ለንጉሥ ወልደጊወርጊስ ሰራዊት ተጨማሪ ድምቀት ሰጥቶት ነበር ። ስለዚህ እጃቢው ሰራዊት ተጉዞ ተከዜን ወንዝ ተሻግሮ በእንደሥላሴ አድርጎ አክሱም ጽዮን ስለደረሰ

ሁለት ትርጉም አለው አንደኛው ከድንቁርና ነጻ መወጣት ሲሆን ሁለተኛው በእግዚያብሔር ጸጋ ከኃጥያት ነጻ መውጣት ነው ።

የተማረ የተመራመረ ለነፍሱ ያደረ በዚህ ዓለም ላይ በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህ የተገኘ እንደሁ ስለሱ ሲል መቅስፍቱ ጥፋቱ በጌታ ስልጣን ይታገዳል ። ለዚህም ማስረጃ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18 ቁጥር 23ና 24 አብርሀምም ቀረብ አለም ጻዲቁን ከኃጥያተኛ ጋር ታጠፋለህን በሀገሪቱ ኀምሳ ጻድቃን ቢገኙ በውኑ ሁሉን ታጠፋለህን ሀገሪቱን አትምርምን ስለሀምሳ ጻድቅ በእርሷ ስለሚገኙ ቁጥር 26 እግዚያብሄርም አለ በሰዶም ሀምሳ ጻዲቅ ባገኝ ባገሪቱ ውስጥ ሀገሪቱን ሁሉ ስለእርሳቸው እምራለሁ ። ቁጥር 28 አርባአምስት ቢሆኑ ስለ አርባ አምስቱ አላጠፋም ። ቁጥር 29 ደግሞም ተናገረ እንዲህም አለ ምን አልባት አርባ ከዚያ ይገኛሉ አለም ስለአርባው ጻድቅ አላጠፋትም አለም ጌታዩ አይቆጣ እኔ ብናገር ምን አለበት ። ከዚያ ሰላሳ ይገኛሉ አለም አላደርግም ከዚያ ሰላሳ ባገኝ አለም እነሆ አንድ ጊዜ ጀመረኩ ከጌታዩ ጋር እናገር ዘንድ ምን አለበት ከዚያ ሀያ ይገኛሉ አለም አላጠፋም ስለኃያው አለም ጌታዩ አይቆጣ እኔ ደግሞ አንድጊዜ ብናገር ምን አለበት ከዚያ አስር ይገኛሉ አለም ስለአስሩ አላጠፋም ።

ከዚህ በላይ በተገለጠው አነጋገር እግዚያብሔር ስለጥቂት ጻድቃን አገርን ከመከራ እንደሚጠብቅና ከጥፋት እንደሚያድናቸው ያስረዳል ። ኃጥያተኞቹ ንስሐ ባለመግባት ጥፋት ቢታዘዝባቸው እንኳን አንድ ብቻ ነው አብሮ ይጥፋ ሳይል ሎጥን እጁን ይዞ በማውጣቱ አስተምሮናል ስለዚህ ቢቻል ብዙ ሰው በኛ ምክንያት የምናድን እንድንሆን ቢታጣ እራሳችን



የምንድንበትን ከፈጣሪያችን ጋር ያለን ግንኙነት እንዳይቋረጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪወች መሆን አለብን እያሉ ያስተምሩ ነበር ።

አለቃ ንዋየክርስቶስ በአክሱምና በአድዋ ለጥቂት ወራቶች ካስተማሩ በኋላ ወደ መቀሌ ተጉዘው በእንደርታ አካባቢ ሲያስተምሩ በደረሱበት ሕዝቡ በማስተናገድ ሲቀበላቸው በሚያረካ የተስፋ መልክት ከብሉይ ከሀዲስ ከቁርአንም እየጠቀሱ ከመንፈሳዊ በረከት ያረኩት ነበር ። በትግሬ ውስጥ የሚገኙ ደጋፊወቻቸው የሰሙት ሁሉ ይህን ስጦታ ለሰው የሰጠውን አምላክ እያመሰገኑ ደስታቸውን ለአለቃ ንዋየክርስቶስ ይገልጡላቸው ነበር ።

በትምህርታቸው የተደሰቱ ብዙ በትግሬ የሚኖሩ ሰወች ክርስትና እየተነሱ የእምነት ተባባሪነታቸውን ስላሳዩ አለቃ ንዋየክርስቶስ ለወደፊት ብሉይ ሀዲስን ሌላውንም ማናቸውንም የሃይማኖት ትምህርት ተምረው መርምረው አውጥተው አውርደው ካጠኑ በኋላ ከእውነተኛው ጋር በመቀላቀል በቀና የጸና እምነት እንዲኖራቸው ሰፋ ያለ ምክር ሰጥተው ከእንደርታ ተነስተው ጣርናና ድህናን ተሻግረው ወደ ዋግ ተጉዘው ሰቆጣ ገቡ ። በዚህን ጊዜ ዋግ ሹምና መኳንንቶቻቸው አለቃ ንዋየክርስቶስን በክብር ተቀበሏቸውና ታላቅ ደስታ ሆኖ ድሮ ከክርስትና በፊት በወገኖቻቸው ተከስው ከዋግ ሹሙ ፊት በቀረቡ ጊዜ አስገራሚ መልሳቸው ሕዝቡን በማስገረሙ ቢደስቱም ደስታቸው ፍጹም ያልነበረው አብረው መብላት አለመቻሉ ነበር ። አሁን ግን ክርስትና ከመነሳታቸው በቀር ንጉሠ ነገሥት ያወቃቸው ሹም ሽልም ሁነው በመቶ ኀምሳ ብረት ታጅበው ሰቆጣ በደረሱ ጊዜ የአለቃ ንዋየክርስቶስ ጸጋና ሞገስ የከበበው ሰውነታቸው በሁሉ

ዘንድ የተረጋገጠ ሰላምና ደስታን ፈጠረ ። ጠብ ሲያረጅ ፍቅር ይሆናል እንደሚባል ሁሉ ወዳጅ ብቻ ሳይሆን በክስ ወደ ባለስልጣን አቅርበዋቸው የነበሩት እነ ሽህ አደም ሳይቀሩ ወደ አለቃ ንዋየክርስቶስ ቀርበው እንኳን ደህና መጡ ብለው ከተገናኙ በኋላ ለዚህ ማእረግ ያበቃነወት እኛ ነን ባንከስና ወደ ባለስልጣን ባናቀርበወት ማን ሊያውቀዎ ይችል ነበረ ። አሁንም መስሎን ብንከራከርም ለወደፊት በየመሰለን በፍቅር እንኖራለን በማለት አነጋገሯቸው ።

አለቃ ንዋየክርስቶስም አምላክ ሲያዝ እንቢ ሲባል የማይቻል ጉዳይ በመሆኑ መልእክቱን በምገልጥበት ጊዜ ወንድሞቸ ብትከሱኝ እውነቱን ለመግለጥ መልስ ብሰጥም ከሳንት ከወንድሞቸ ምንም ቂም የለኝም እናንተ ያደረጋችሁት ሁሉ የቀና መስሏችሁ እንጅ በተንኮል አልነበረም ። ይህንንም እኔ እራሴ ከነብሳታ ኪዳነማርያም ጋር ፈጽሜው ነበር እኔም እንዲሁ የፈጸምኩት መስሎኝ እንጅ በእውቀት አልነበረም እሱው ተገልጦ የምሰራውን ከገለጠልኝ በኋላ ግን ሰው የጠላሁበትን ጉዳይ እራሴ የተጣላሁበት ጊዜ አልፎ ጊዜ ሲጠጋ ሁሉ ለመልካም ሁኖ ተገኘ ። እንዳላችሁት ከሳሽ ተከሳሽ ሁነን ባንቀርብ ማን ያውቀን ነበር ካልተዋወቅንስ እንደምን ከማእረግ ለመድረስ ይቻል ነበር ። በችግር ተዘርቶ በደስታ መከር እንዲሚሰበሰብ ሁሉ ብረትና ብረት ሲያጋጩት ስለት እንደሚገኝ ሁሉ በተደረገው ክርክር ብዙ እውቀት ከማግኘታችንም በላይ እንዳሉት ክብርና ማእረግም ማስገኘቱ የማይካድ ነው ።

በመጨረሻም ከሳንት ከወንድሞቸ ጋር እንዲህ በሰላም መነጋገሬ ለኔ ታላቅ ደስታ ሰጥቶኛል መጥታችሁ በመጎብኘታችሁና በመገናኘታችን



እግዚያብሔር ይስጥልኝ ብለው መለሱላቸውና ታላቅ ደስታ ሆነ መኳንንቱና ዋግ ሹሙ ድግስ እየደገሱ አለቃ ንዋየክርስቶስን ካስደሰቷቸው በኋላ እሳቸውም በዋግ በደህና ለሁለት ወር ያክል እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ እያሉ ሕዝብ ወደ ክርስትና በመደባለቃቸው ለሰላምና ለፍቅር ታላቅ በር ተከፈተ ተለያይቶ ይኖር የነበረው ሕዝብ አሁን አብሮ በመብላት ከመደስቱ በቀር ባበልጅነትና በጋብቻ በመተሳሰሩ ምክንያት ለአንድነት መድህን ተገኘለት ።

አለቃ ንዋየክርስቶሰ በዚህ ጊዜ ለጋብቻውና በየማህበሩ እየተገኙ የአንድነትንና የመተባበርን ጥቅም እንዲህ እያሉ ያስተምሩ ነበር ። "በአንድነት ይሰራል ቤት፤ በመለያየት ይፈርሳል ቤት፤ ቤት ሲሰራ የሀገር መሰረት ይጸና ። ልጅ ይወለዳል ለሰው መኖር መሰረቱ ይህ ነው ። ሁለት የትዳር ጓደኞች አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ ተባብለው የተደጋገፉ እንደሁ ከባድ የትዳር መቋቋም ስራ በመጽናት ልጅ የሚያሳድግ ሽማግሌ ባልቴት የሚጠውር ሲመሽ የሚያሳድር ሲገድ የሚያበድር ያገር ሽማግሌ አባውራ በአደባባይ ሰው ሲጣላ የሚያስታርቅ ይገኛል ።

በአሞጽ ምዕራፍ 3 ቁጥር 3 በውኑ ሁለት ሰወች ያለስምምነት በአንድ ይሄዳሉን ? ይላል ይህ ለአንድነት ማሃስረጃ ታላቅ ጥያቄ ነው ። ሁለት ሰወች ሲስማሙ ኮሳሶች ቢሆኑ አንድን ብርቱ ሊያጠቁ እንደሚችሉ እንዲህ ይባላል ለአንድ ብርቱ ሁለት ኮሳሳ መድሃኒቱ ይህም አንድ ብርቱ ሁለቱን ኮሳሶች ሊያጠቃ አይችልም ማሃለት ነው ። አንድ አባት ልጆቹን ጠርቶ ስለ አንድነታቸው አስፈላጊነት ሲያስተምር ሁለት ሁለት ብትር ቆርጣችሁ አምጡ አሳቸው ።

ልጆቹም እንደታዘዙት አመጡ አባትየው ለልጆቹ እንዳንድ በትር ስጡኝ አለና ተቀብሎ ከአንድ ላይ አስራቸውና ልጆቹን በየጻቸው ያለውን እንዳንድ በትር እያንዳንዳቸው እንዲሰብሩ ጠየቃቸው እነሱም በቀላሉ ሊሰብሩት ቻሉ። ከዚህ በኋላ ከአንድ የታሰሩትን ብትሮች ከትንሹ ጀምሮ እስከ ትልቁ እንዲሰብሩ አዘዛቸው ሁሉም እያንዳዳቸው ቢሞክሩ ለመስበር ላይቻላቸው ቀረ ። አባትየውም እዩት አንድነት ለሕይወት ምን ያህል ተፈላጊ እንደሆነ ሲሉ መከሯቸው ይባላል ።

ይህ አንድነት በሃይማኖት አለም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህም በገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 26-28 እላንተም ሁላችሁ የእግዚያብሔር ልጆች ናችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት እላንትም ሁላችሁ በክርስቶስ የተጠመቃችሁ ክርስቶስን ለብሳችሁ በዚህም አይሁዳዊ የለም አረማዊይም ባርያም የሰው ልጅም ወንድም ሴትም እላንት ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ ።

ከአንድ ደም የተሰራው የሰው ልጅ ወንድማማችነቱ በዳቢሎስ አሳሳችነት ቀርቶ በጠብ ስለተለያዩ ልዩ ልዩ ባህልና ልማድ እያስገደደው እርስ በእርሱ ሲያፋጀው በመኖሩ እርቅና ሰላም ፍቅር አንድነትና ስምምነት እንዲያገኝ በማስተማር ኢየሱስ ክርስቶስ እረቂቅና ጥልቅ በሆነ መለኮታዊ ስልጣን ሰው ሆኖ ተገለጠ ። እሱም የተጣሉትን በማስታረቅ የተለያዩትን በማገናኘት ለሰው ልጆች የአንድነት መሰረት ጣለላቸው ።

ዘፍጥረት ምዕራፍ 28 ቁጥር 12ና13 ህልምም አዩ እነሆ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ እሱም ወደ ሰማይ ደርሶ እነሆም የእግዚያብሔር መልክተኛ ይወጡ ይወርዱበት ነበር ። እነሆ እግዚያብሔር በላዩ ቆሞ ብሎ ነበር ።



እግዚያብሔር ከሰማይ ያእቆብ ከምድር ሆነው ያእቆብንና እግዚያብሔርን ያገናኙ ይመስላል ። ኃጥያተኛዋን አለምና እግዚያብሔርን በማስታረቅ ያገናኘው የኢየሱስ ምሳሌ ነው ። በዚህ እርቅ ምክንያት የሚድኑትን ለማስታረቅ መሰላል ምሳሌ በሆነለት በየኢሱስ መላእክት ይወጣሉ ይወርዳሉ ። ከላይ የተሰፋ መልእክት ይዘው ሲወርዱ ከታች የሰውን ስራ መረጃ ወደ ሰማይ ይዘው ይሄዳሉ ።

ሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 10 ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ሳለ በልጁ ሞት ከእግዚያብሔር ጋር ታርቀናል አሁንም ከእግዚያብሔር ጋር ከታረቅን በኋላ በሕያው ልጁ አማካኝነት ይበልጡን እንድናለን ። ለወደፊቱ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ሮሜ ምዕራፍ 12ቁጥር 10 በክርስቶስ ወንድማማቾች እንደመሆናችሁ መጠን እርስ በእርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ እርስ በእርሳችሁ ለመከባበርም ተሽቀዳደሙ ።

እብራውያን ምዕራፍ 13 ቁጥር 1ና2 ሁልጊዜ የወንድማማችነት ፍቅር ይኑራችሁ እንግዳ ተቀብሎ ማስተናገድን አትርሱ ምክንያቱም እንደዚህ እንግዶችን እየተቀበሉ በማስተናገድ አንዳንድ ሰዎች ሳያውቁ መልአክትን ተቀብለው አስተናግደዋል ። እያሉ ሲያስተምሩ አለቃ ንዋየክርስቶስ የተጠሩበትን ተግባር በዋግ በድህና ሰፋ ያለ የረቀቀ የጠለቀ ሚስጥር እየገለጡ አስተማሩ ።

ከስቆጣ ተነስተው አመድወረቅን አድርገው ስራ ከጀመሩበት በሲልዳ ቀበሌ ላማ በደረሱ ጊዜ ሕዝቡ ጥሩ አቀባበል እያደረገ የናፈቃቸው ሁሉ አስደስታቸውና እምላካቸውን አመስግነው መረብን ተሻግረው ራእይ

ወደተቀበሉበት እናቡግና ቀበሌ ጣርና ደረሱ ። የላስታ ሕዝብ በናፍቆት በፍቅርና በደስታ ተቀብሎ ስሜቱን ሲገልጥላቸው ተናግረው በማይሰለቸው እንደበታቸው እንደገና ያረኩት ጀመር ። ከያለበት እየመጣ ቆየት ብለው እንዲያስተምሩት እየጠየቀ ቢያስቸግራቸውም ቤተሰቦቻቸው ከነገላ ወደ ጣርና መጥተው ከተቀበሏቸው በኋላ ቤተሰቡ በሙሉ በጣም ፊታቸውን ለማየት መቸኮላቸውን ስለስሙ ከጣርና ተነስተው ነገላ ሰኞ ገቢያ ከቤተሰባቸው ደረሱና ደስታ ሆነ ።

አለቃ ንዋየክርስቶስ ከቤታቸው ብዙም ጊዜ አይቆዩም ነበር ። ወደ ደብረታቦርና ወደ መልዛ ወደ በለሳ እስከ ጎንደር እየተጓዙ ክጌታ የተጠሩበትን አገልግሎት ስህተት ሳይጨመርበት ወይም ሳይቀንሱ ብሉይና ሀዲስን ቁርአንንም በደንብ አስተውለው በመማርና በማስተማር ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር ።

በ1909 እ.ም በሰገሌና በደሴ ላይ በተደረገው ጦርነት የንጉሥ ወልደ ጊወርጊስ ሠራዊት ሲዘምት አብረው ዘምተው ሠራዊቱን በምክር እየደገፉ በመንፈሳዊ መንገድ ለሚደረገው ያገር አገልግሎት በትግስት ሲፈጽሙ ከጦርነት ላይ ሰዎቻቸው ስለተጋፈጡ ጀግኖች ደጋፊወቻቸው እየማረኩ ሲመለሱ ከምርኮኞቹ መካከል ትርኮችም ይገኙበት ነበር ። ስጋ ወድቆ አፈር ሳይዝ አይነሳም እንደሚባል ሁሉ የወንድማቸው ልጅ ዳወድ ይሳ የተባለው ከጦርነቱ ላይ ስለወደቀ በክብር ጓደኞቹ አንስተው ወደ አለቃ ንዋየክርስቶስ ድንኳን ስላመጡት አለቃ ነዋየክርስቶስም የአገር ፍቅር መስዋእትነትን መጠየቁ የታወቀ ነው ጌታም ከኃጥያት ባርነት ነጻ ያወጣን በደሙ ስለሆነ ሰላም ለማግኘት በተደረገው ጥረት ደም ቢፈስ እምላክን ልናማርረው አይገባንም ብለው በክብር አስቀበሩት ።



በዚህ እኳኋን ደሴ ደርሰው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ከደሴ እስከ ጎንደር ለሚገኘው ሕዝብ ከመለያየትና እርስ በእርስ ከመዋጋት ይልቅ በአንድነት መንፈስ በመመካከር ተደጋግፎ መኖር ይበልጥ እንደሚጠቅም እየገለጡ እግዚያብሔርም አንድነትን የሚወድ መሆኑን ፍቅርና ሰላም ለአገር እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን እያስተማሩ ተመለሱ ።

አለቃ ንዋየክርስቶስ ከሰገሌ መልስ በነገላ ቤታቸው ለሶስት አመታት ያህል እያስተማሩ ከቆዩ በኋላ በ1912 በሰኔ ወር ደብረታቦር ድረስ የቻለ ሁሉ መጥቶ የመጨረሻ ጊዜ ምክራቸውን እንዲቀበል በያገሩ መልክተኛ ላኩ የሚናገሩት ቃል ተደማጭነቱ የሚፈጸም መሆኑን ሁሉ ስለሚያውቀው ነበር ። አሁንም ጊዜየ ስለተቃረበ ኑና እንስነባበት የሚል ቃል በመልክቱ ስለነበረበት እጅግ በጣም የሚወዳቸው ሕዝብ ታላቅ ሽክም ወደቀበት እና በተወስነው ጊዜ ደብረታቦር ላይ ተሰብስቦ ሲጠባበቃቸው ከነገላ ተነስተው ደብረታቦር ደረሱ ምንም እንኳ ሲያዮዋቸው ደስ ቢላቸውም በልቡ ያልደነገጠ ሰው አልነበረም ዜና እረፍታቸውን የሚገልጠውን መልእክትና ከእረፍታቸው በኋላ ምእምናኑ ምን መከተል እንደሚገባቸው ለተከታዮቻቸውና ለደጋፊወቻቸው ስፊ ማብራርያ ለመስጠት በመጡ ጊዜ አቶ ያሲንና ጎረቤቶቻቸው ፍሪዳ አርደው ደግሰው ተቀበሏቸው ።

ለቅስጠት ምን ጊዜም ቅርብ ነው ለዚሁ የስጠው ተስፋ የሚከተለው ነው ።

ዘሁልቅ ምዕራፍ 12 ቁጥር 6 አላቸውም ነገሬን ስሙ በመካከላችሁ ነብይ ሰው ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገልጥለታለሁ ወይንም በህልም እናገረዋለሁ ።

አሞጽ ምዕራፍ 3 ቁጥር 7 እግዚአብሔር ነገር እያደርግምና ሚስጥሩን ለባሮቹ ለነበያቶች ካልነገረ ሲል በታላላቅና በታናናሽ ነበያት እየገለጠ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሚስጥር ሲገልጥ የኖረው አምላክ እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ዘመን በሚከተለው አኳኋን እየገለጠ ሲያዋያቸው ነበረ ።

የሐዋርያት ስራ ምዕራፍ 9 ቁጥር 3-7 ጳውሎስ የሰማይ ብርሃን ተቀብሎ ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ ይህ ለጳውሎስ የመጀመርያ ራእይ ነበር ። ይህ ራእይ ለጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ለሐናንያ በምዕራፍ 9 ቁጥር 10 ና 11 በራእይ አዘዘው ለጳውሎስም በምዕራፍ 22 ቁጥር 14 እስከ 16 ሀናንያን እንዲህ አለው ። ያባቶቻችን አምላክ አስቀድሞ መረጠህ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድ የጻዲቁንም ታይ ዘንድ ካፉም ድምጽ ትሰማ ዘንድ በሰውም ሁሉ ፊት ምስክር ትሆንለታለህ ባየኸውም በሰማኸውም ስራ ሁሉ አሁንም ምን ትዘገያለህ ተነሳና ተጠመቅ ኃጥያትህንም ታጠብ የጌታን ስም ስትጠራ ብሎ አስረዳው ጳውሎስም ይቃወመው የነበረውን ስራ እሱ እንዲያስተምር አምላካዊዩ ራእይ ጠራው ለተጠራበት ተግባር እስከ ሞት ድረስ የታመነ ሆነ ።

በራእይ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 1-3 የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ እግዚአብሔር የስጠው ፈጥኖ



የሚሆነውን ነገር ለባሮቹ ይገልጽ ዘንድ አመለከተው በመላኩ እጅም ወደ ባርያው ወደ ዮሐንስ ላከው ለእግዚአብሔር የመስከረ ለኢየሱስ ክርስቶስም ምስክር ባየው ሁሉ ነገር ምስጋና ይገባዋል ለሚያነብ የዚህን ትንቢት ነገር ለሚሰሙ በእርሱ የተጻፈውንም ለሚጠብቁ ዘመን ቀርቧልና ።

ዮሐንስን የእግዚአብሔርን አገልጋይ ባስገራሚው ራእይ ኢየሱስ አበለጸገው ክርሱ የሚገኘውን ሚስጥር ለመረዳት እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሮች መሆን ያሻናል ። ስለዚህ ልንጠነቀቅ ይገባናል ሚስጥሩ ከመርቀቁ የተነሳ ብዙወቹ ከመጠራጠር ይደርሳሉ ዳሩ ግን ለተመረጡት እውነተኛ የጊዜው መልክት ነው ።

እለቃ ንዋየክርስቶስ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም እነዚህን የመሰሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ስለ ራእይ ስጦታ እየገለጡ ካስተማሩ በኋላ ስለራሳቸው እንዲህ ብለዋል ።

በኢትዮጵያ በሃይማኖት ምክንያት ከበድ ያለ አለመግባባት በሕዝቡና በመንግስቱ መካከል በተቀስቀሰበት ጊዜ ይህን ለማስወገድ የሰማይ አምላክ የራእይ ስጦታ ይዞ እኔን አንድ ምስኪን ድሀ ካለሁበት ጎበኘኝ ።

እንዲህም አለኝ ዘካርያስ የእግዚያብሄር ባርያ ወደኔ ቅረብ አለኝ እኔም እሽ አልኩት ከራሴም ላይ እፍ አለብኝ እስከ እግረጫማየ ተሰማኝ ቆየት ብየም በታላቅ ሀሳብ በምጨነቅበት ጊዜ ሶስት ተመሳሳይ አካል ከመካከላቸው አስቀምጠው ልጃችን ዘካርያስ አይዞህ አትዘን ትርጉም ልንነግርህ መጥተናል የበረታህ ሁን እኛም አንለይህም የአራቱን የወንጌሉን ቃል

አስተካክለው በትክክል ተርጉመው እያሉ በብዙ መክረውኝ እንድ አካል ሁነው ሄዱ እነሱን ተከትሎ የተገለጠልኝ ደመናና ዝናብ በጥቅምት ለተገኘው አዲስ ልደት የሚዘንበው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሆነ ተነግሪያለሁ ።

በዚህ መሰረት ሥራውን ስጀምር በእርግጥ ጌታ አብሮን እስካሁን ለመኖሩ እላንት ምስክር ናችሁ ። በነዚህ 27 አመታት በትግሬ በዋግ በላስታ በበጌ ምድር በወሎ በጎጃም በሸዋ እየተጓዝን ባደረግነው መንፈሳዊ ዘመቻ ራሱ ያልተለየው ጥረት በመሆኑ ይኸው ከእስር ሽህ በላይ የሚሆኑት የአለም መድሃኒት የሆነውን ጌታ በማወቅ የእምላክ ልጅነት ጸጋ ተጎናጸፉ እላንትም ከነርሱ መካከል ስለሆናችሁ ደስ ይበላችሁ እንጅ የምትደነግጡበት ምክንያት የላችሁም ።

እግዚአብሔር ላገልግሎት የጠራቸውን በመንፈሱ ሚስጥር ሲገልጥ የሚመጣ ነገር ሁሉ አይስወርባቸውም ሌላው ሁሉ እንደሚገለጥላቸው ዜና እረፍታቸውም ይገለጽላቸዋል ። ይህም በመደንገጥ ፈንታ ለዝግጅት እንዲጠቅማቸው ነው ። ዜና እረፍታቸው ሲገለጥላቸው ሙሴ ለዝግጅት ሲጠቀምበት ሕዝቅያስ የእይሁድ ንጉሥ ግን በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 20 ቁጥር 21 ዜና እረፍቱን በሰማ ጊዜ በጣም እንዳዘነ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 32 ቁጥር 24-31 ኢሳያስ ምዕራፍ 39 ቁጠር 1-8 ይናገራል ። አምላክ ጸሎቱን ሰምቶ 15 አመታት ሲጨመርለት ከሞት የፈወሰውን እምላክ አክብሮ በማስከበር ፈንታ ስለመፈወሱ ደስታቸውን ለመግለጽና ከዋክብትን የሚያጠኑት ባቢሎናውያን ከዋክብት እንዲህ የሆነችው ፀሐያችን ከዚያ በፊት የማያውቁት ከዚያ በኋላ ያልተደገመ ወደ ኋላ መመለስዋ በምን ታምር እንደሆነ ለማወቅ በሚገኙበት ጊዜ እግዚአብሔር የይሁዳን ንጉሥ



ለመፈወስ የሰጠው ምልክት መሆኑን በመስማታቸው ስለዚሁ ታምር ስራ ለማወቅ የመጡትን የባቢሎን መሳፍንት በስንሄሰረብ ሰራዊት 180 ሽህ ወታደር በአንድ ሌሊት የጨረሰለትን ቢታመም በታምር የፈወሰውን አምላክ ከባቢሎናዊያን ነገሥታትና ሕዝብ ጋራ በማስተዋወቅ ፈንታ እግዚአብሔር ለእርሱ ቢሰጠው ባምላክ ስፍራ ያስቀመጠውን ሀብቱን እሳያቸው ያዩ ባቢሎናዊያን የይሁዳን ነገሥታት ሐብትና ንብረት ለመማረክ ምኞት አሳደረባቸው ይህ ምኞታቸው ገፋፍቷቸው ቅድስት አገርን መጥተው ሲበዘብዙ ሐብት ብቻ ሳይሆን የነገሥታቱን ልጆች ሁሉ ማርከው ወሰዷቸው ። የዚህ ሁሉ ጥፋት ሰረመሠረቱ የሕዝቅያስ እግዚአብሔርን እረስቶ በሀብቱ መታመን ያመጣው ጣጣ ነው ። ስለዚህ ሁሉ አምላክ ወስኖ በሰጠው ጊዜ በታማኝነት ሰርቶ ባለው ጊዜ ለእረፍት ቢዘጋጅ የተሻለ ነው ። ጌታ የወሰነው ጊዜ የበለጠ እንደሚጠቅም አምናለሁ ።

ሙሴ የእግዚአብሔር ባርያ የሚሞትበትን ጊዜ ፈጣሪ በገለጸለት ጊዜ በመደንገጥ ፈንታ እሱ ከተዘጋጀ በኋላ ለሚቱ የሰው ልጅ ሁሉ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ሰጠ ።

ዘዳግም ምዕራፍ 28 ቁጥር 1-14 በረከትን ከቁጥር 15-21 መርገሙን ጽፎ እስከ ምዕራፍ መጨረሻ መርገሙ ይቀጥላል ። ከቁጥር 1-21 ያለው የሚከተለው ነው ።

የእግዚአብሔርንም ያምላክህን ቃል የሰማህ እንደ ሆነ ዛሬ እኔ የማዝህን ትዛዙን ሁሉ ለማድረግ ለመጠበቅም እግዚአብሔር እምላክህ በምድር ካሉ ከእህዛብ ሁሉ በላይ ያደርግሀል ።

ይህችም በረከት ሁሉ ትወርድብሀለች ታገኝሀማለች የእግዚአብሔርን የአምላክህን ትዛዝ የሰማህ እንደሆነ አንተ ባገር የተባረክህ ትሆናለህ ። ብርህም የተባረከ ይሆናል ። የሆድህ ፍሬ የተባረከ ይሆናል የምድርህም ፍሬ የከብትህም ፍሬ የላምህም መንጋ የበጎችህም ማራባት እንቅብህ የተባረከ ይሆናል ። የብሆ እቃህም አንተ በመግባትህ የተባረክህ ትሆናለህ በመውጣትህም አንተ በረከት ይሆንልሀል ። እግዚአብሔር የሚጠሉህን ጠላቶችህን በፊተና ተመቾች ያደርጋቸዋል ። በአንድ መንገድ ወዳንተ ይመጡብሀል በሰባት መንገድ ከፊትህ ይሸሻሉ እግዚአብሔር በረከቱን በአንተ ላይ ይሰዳል በጎተራህ በጅህም ስራ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ይባርክሀል ። እግዚአብሔር ለሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሀል እንደማለልህ የእግዚአብሔርን ትዛዝ ብትጠብቅ በመንገዱም ብትሄድ በምድርም ያሉ አሕዛብ ሁሉ የእግዚአብሔር ስም እንደተጸራብህ ያዩሀል ይፈሩሀማል እግዚአብሔር በጎነቱን ሁሉ በላይህ ያፈሰዋል ። በሆድህ ፍሬ በእንሰሶችህ ፍሬ በእርሻ ፍሬ በምድር ላይ እግዚአብሔር ላባቶችህ በማለላቸው እርሷን ይሰጥህ ዘንድ እግዚአብሔር ሰማዩን ይከፍትልሀል ። መልካሙን መዝገቡን የምድርህን ዝናብ በወራቱ ይሰጥህ ዘንድ የእጅህንም ስራ ሁሉ ይባርክ ዘንድ ። ለብዙ አሕዛብ ታበድራለህ አንተ ግን ከማንም አትበደርም ። እግዚአብሔር ለራስ ያደርግሀል ለጅራትም አይደለም ሁልጊዜ በላይ ትሆናለህ በታችም አትሆንም ዛሬ እኔ የማዝህን የእግዚአብሐር የአምላክህን ትዛዝ የሰማህ እንደሆን ብትጠብቃትም ብታደርጋትም ከዚችም ትእዛዝ ሁሉ ዛሬ እኔ ከማዛችሁ ወደቀኝ ወደግራም ባትል እንግዶችን አማልክት ትከተል ዘንድ ታመልካቸውም ዘንድ ።



የእግዚአብሔርን የአምላክህን ቃል ግን ትሰማ ዘንድ ባትወድ ትእዛዙንም ሁሉ ለመጠበቅ ሕግንም እኔ ዛሬ የማዝህን ይህች መርገም ሁሉ ትጠብቅሀለች ታገኝሀማለች ። በከተማ እርጉም ትሆናለህ በእርሻ እንቅብህ እርጉም ይሆናል ። የብሆ እቃህም የሆድህ ፍሬ እርጉም ይሆናል ። የእርሻህም ፍሬ የላምህም መንጋ የበጎችህም ማርባት አንተም በመግባትህ የተረገምህ ትሆናለህ በመውጣትህም መርገም ይሆንብሀል ። እግዚአብሔር መርገም ድብልቅልቅ ተግሳፅም ይሰድብሀል በምትሰራው ስራ ሁሉ እስክትጠፋ ድረስ ፈጥኖም እስከታላቅ ድረስ ስለክፉ ስራህ እኔንም ስለተውከኝ እግዚአብሔር ቸነፈር ያጣብቅብሀል ልትወርሳት ከምትገባባት ምድር እስኪያጠፋህ ድረስ ።

ዘዳግም ምዕራፍ 31 ቁጥር 2,6,8,9,15፣16 ምዕራፍ 32 ቁጥር 1,7-14 ,46-50 ሙሴም ሄደ ይህንንም ነገር ለእስራኤል ሁሉ ነገረ አላቸውም እኔ ዛሬ 120 አመት ሆነኝ ከዚህ በኋላ እወጣ እገባ ዘንድ አልችልም እግዚአብሔር ይህን ዮርዳኖስን አሻገረ አለኝ ጽኑ በርቱ አትፍሩ ከፊታቸው አትደንግጡ እግዚአብሔር አምላክህ ካንተ ጋር ይሄዳልና አይጥልህም ። እግዚአብሔርም እርሱ በፊታችሁ የሚሄደው እርሱ ካንተ ጋር ይሆናል አይተውህም ቸልም አይልህም አትፍራ አትደንግጥም ሙሴም ይህችን ሕግ ጻፈ ለካህናትም ለሌዊ ልጆች የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ድንኳን ይሸከሙ ለነበሩት አሳልፎ ሰጣቸው ለእስራኤል ሽማግሎች ሁሉ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው የምትሞትበት ቀን እነሆ ቀረበ እያሱን ጠርተህ በማህበሩ ድንኳን ከርሱ ጋር ቁም እሱን አዝዘው ዘንድ እያሱና ሙሴም ሄዱ በማህበሩ ድንኳን ቆሙ እግዚአብሔርም በድንኳኑ

ተገለጠ በደመና አምድ የደመናው አምድ በድንኳኑ ደጅ ላይ ቆመ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው እነሆ አንተ ካባቶችህ ጋር ትተኛለህ ።

እላንት ሰማዮች አድምጡ እኔም እናገራለሁ ። ምድርም ያፌን ነገር ትስማ የድሮውን ነገር አስብ የልጅ ልጅህንም አመታት አስተውል አባትህን ጠይቅ ይነግርህማል ሽማግሎችህ ይሉህማል ልዑል እርስትን ለአህዛብ በከፈለ ጊዜ የአዳምን ልጆች በለየ ጊዜ የሕዝብን ጉልት እንደ እስራኤል ልጆች ቁጥር አቆመ ። የእግዚአብሔር ፈንታ ሕዝብ ነውና ያእቅብም የርስቱን ገመድ በምድረ በዳ አገኘው በጽማት በውድማም ስፍራ ውሽት በመላበት ከበበው ተጠነቀቀለትም እንደ ዓይኑ ብሌን ጠበቀው ። ንስር ጫጩቶቹን እንደሚያወጣ በእርሳቸውም ላይ እንዲሰፍን ክንፉን ዘርግቶ ይወስዳቸዋል በደረቱም ይሸከማቸዋል ። እግዚአብሔር ብቻውን መራው ከእርሱም ጋር ሌላ አምላክ አልነበረም ። በምድር ክፍታ ላይ አወጣው ። የርሻውንም እህል በላ ከድንጋይ በሚገኝ ማር አጠበው በዘይትም በጽኑ ድንጋይ በላምም ቅቤ በበግም ወተት ከጥቦት ስብ ጋር በባላንም ዳንግሲ ቁርንቢም ከስንዴ እሸት ጋር የወይንም ደም ጸጅ እየፈላ ጠጣህ ።

አላቸውም ዛሬ እኔ የምመሰክርላችሁን ነገር ሁሉ በልባችሁ እሰሩት ። ልጆቻችሁን ታዙበት ዘንድ እንዲጠብቁት በዚህም ሕግ የተጻፈውን ሁሉ እንዲያደርጉት ይህ ነገር በከንቱ አይደለምና ሕይወታችሁ ነው እንጅ ። ይህነንም ነገር በማድረግ እረጅም ዘመን ትቀመጣላችሁ። ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ በምትገቡባት ምድር ትወርሷት ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን በዚያ ቀን ዳግም ተናገረው አለውም ወደ



አበሪም ተራራ ውጣ ወደ ነቦ ተራራ በሞአብ ምድር ወዳለው በያሪኮ አንጻር ለእስራኤር ልጆች እርስት አድርጌ የምሰጣቸውን የከንዓንን ምድር እይ በወጣህበትም ተራራ ሙት ወደ ዘመዶችህም ትከማቻለህ ።አሮን ወንድምህ በሆር ተራራ እንደ ሞተ ወደ ወገኖቹ እንደተከማቼ ።

ለሙሴ ዜና እረፍቱ በሰማይ አባቱ አንደበት በተነገረው ጊዜ በዘዳግም ምዕራፍ 31 ቁጥር 16 እነሆ አንተ ካባቶችህ ጋር ትተኛለህ ። ነው የተባለው አንድ ሰው ብርቱ ስራ ሲሰራ ከቆየ በኋላ ድካም ሲሰማው ወዳጆቹ ገደም ብለህ ተኝተህ እርፍ ብለህ ተነሳ ብለው እንደሚነግሩት ሁሉ እግዚአብሔር አብ ሙሴን ትተኛለህ የሚለውን አምላካዊዩን ድምጽ ባሰማ ጊዜ ለምን ለእረፍት ተኛ ይለኛል ብሎ አላጉረመረመም ለእረፍት ወደ ተመደበለት ቦታ ወደ ኔቦ ተራራ ሄዶ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ በዛ ተኝቶ ቆየ ። ዘዳግም ምዕራፍ 34 ቁጥር 5-7 ስለዚህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በሞአብ ምድር ሳለ በዚያ ሞተ ። እግዚአብሔርም ከቤትፐዖር ከተማ ፊት ለፊት በሞአብ አገር በሚገኘው ሸለቆ ቀበረው ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ እርሱ የተቀበረበትን ትክክለኛ ስፍራ ለይቶ የሚያውቅ የለም ። ሙሴም በሞተ ጊዜ እድሜው 120 አመት ነበረ ።

በራእይ ምዕራፍ 1 ቁጥር 18 ህያው ሙቸ ነበርኩ እነሆ ህያው ነኝ ። ለዘለዓለሙ አሜን ። የሲኦልና የሞት መፍቻም ከኔ ጋር ነው ብሎ በተናገረው መሰረት የመቃብርና የሞትን መክፈቻ ስልጣን ጨብጦ መድዓኒአለም ሊቀመልአክት ሚካኤል በተባለ የመላእክት አለቅነት ስልጣኑ የሙሴን መቃብር ከተኛበት ለመቀስቀስ ሲጎበኝ የሰው ልጆች ጠላት

የሆነው ሰይጣን የሙሴን ስጋ መነሳት የለበትም ሲል በይሁዳ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ ስለሙሴ አስክሬን ከዲያቢሎስ ጋር በብርቱ በተከራከረ ጊዜ "እግዚአብሔር ይገስጽህ!" አለው እንጅ የስድብ ቃል በመናገር ሊፈርድበት አልደፈረም ። ሙሴም ለመነሳቱ በማቴወስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 2 በፊታቸውም ተለወጠ ፊቱም እንደ ፀሀይ አበራ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ ። እነሆም ሙሴና ኤልያስ ለእርሳቸው ታዩ ከእርሱም ጋር ሲናገሩ ስለሚል ሙሴ ከእንቅልፉ ነቅቶ መነሳቱን ስለሚያረጋግጥልኝ ። እኔም በክብር በመተኛት ወደ እረፍት የምሄድበትን ጊዜ ስላረጋገጠልኝ በስጋ በመካከላችሁ ለመገኘት ይህ የመጨረሻው ምዕራፍ ስለሆነ እኔም ለናንተ ላስረዳችሁ የምወደው ያነኑ ደግሜ ነው ። ብትታዘዙ በረከትን ብታምጹ ሰይፍን መርገምን በደመወዝ ታገኙታላችሁ ። ኢሳያስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 19ና 20 እሽ ብትሉ እኔንም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ ። እቢም ብትሉ ብታምጹ ሰይፍ ይበላችኋል ። የእግዚአብሔር አፍ ተናግሯልና ይላል ። በመታዘዝ ክሕጉ ጋር በደንብ መተዋወቅ ያስፈልጋል ሕጉን ለመታዘዝ መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠኑ እረቂቅና ጥልቅ የሆነ ብዙ መንፈሳዊይና ስጋዊ እውቀት ስለሚያስገኛችሁ ለወደፊት በሚቀጥለው ትውልድ የሕይወት ትርጉሙ የሚያገኘውም ችግር መፍትሄው እውቀት ሆኖ ታገኙታላችሁ ። በእውቀትና ባለእውቀት በመማርና ባለመማር መካከል ያለው ልዩነት በብርሃንና በጨለማ መካከል ካለው ልዩነት ይብሳል ። ስለዚህ መማርን ቸል እንዳትሉ የተማረ የተመራመረ ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገረ ያልተማረ በጨለማና በሞት ወንዝ ቀረ ይባላል ። እኔ ለማስተማር የሞከርኩ እጅግ አነስተኛ በሆነ መንገድ ነው ። የጽሁፍ መሳርያ ቀለም ችግር በመሆኑ እንጨት እየጠረብን ከዚያ ላይ በመጽሐፍ የግራር ሙጫ በጥላት እየቀለምን



በሸንበቆ ብዕር በበግና በፍየል ብራና እየጻፍን የተማርነውና ያስተማርነው ለወደፊት ለሚነሳው ትውልድ መሠረት ለመጣል እንጅ በቂ ሆኖ አልነበረም ። ስለዚህ እኔ ጀማሪ ነኝ ይህን ከግቡ የሚያደርሱት ልጆቻችን ናቸው ። አሁን ስማቸውን በጠራሁት ነበር ዳሩ ግን ችግርን እንዳይፈጠርባቸው መናገር አስፈላጊ አይደለም ። አላንት ታላላቆቹ ትፈራላችሁ ግን ህጻናቶቹ አይፈሩም ምልክት ልስጣችሁ በመንፈሳዊም ሆነ በስጋዊ ጠለቅ ብለው ያወቁ ቋንቋቸው ልዩ የሆነ አንድን የእግዚአብሔርን ቃል በሶስት ቋንቋ እንደተናገረ ሁለቱ ተርጓሚ በየቋንቋቸው ሶስት ሆነው ቆመው ሲሰብኩላችሁ ትክክለኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሀሊናችሁ እንዲቀበለው አድርገው ሲናገረው ትሰማላችሁ ። በዚህ ጊዜ መማር የቋንቋንም ችግር ስለሚያስወግድ ሁሉም ግልጽ እንዲሆን እናንተና ልጆቻችሁ ትምህርትን ችላ እንዳትሉ አደራ እላችኋለሁ ። ስትማሩ ስትመራመሩ ችግር ይገጥማችኋል ። ራእይ ምእራፍ 10 ቁጥር 9 ወደ መላኩም ሄድሁ እልሁትም ታናሹን መጽሐፍ ስጠኝ አለኝም ውሰደው ብላውም ሆድህንም ያምርረው ባፍህ ግን ጣፋጭ ይሁን እንደማር ።

ዮሐንስ ወስዶ የበላው መጽሐፍ ቅዱስን ነው መብላቱም መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናቱን ያሳያል እንጅ ወረቀቱን እያላመጠ መዋጥ አልነበረም የእግዚአብሔር ቃል ባጠናው ጊዜ እንደማር ቢጣፍጠውም ለሌሎች በሚያስተምርበት ጊዜ መራራ ስደት አስነስቶ በጳጢሞስ ደሴት እንዲታሰር አደረገው ።

እግዚአብሔር በብሉይና ሃዲስ የሰጠው ስልጣን በሰዎች አማካኝነት ስለሚነገር እንዲህ ይላል ። ራእይ ምዕራፍ 11 ስልጣንም እሰጣለሁ ለሁለቱ ሰማእታቴ

ሽህ ከሁለት መቶ ስልሳ ቀንም ትንቢት ይናገራሉ ማቅ ለብሰው ::

እውነት ሲነገር ስደት መነሳቱ ከጥንት የቆየ በመሆኑ ዛሬም እውነትን ለማጥናት ከተዋወቃችሁ በኋላ እውነትን እንድታደርሱ መልክታችሁን ስታስተምሩ ስደት ሲነሳባችሁ አትደንግጡ ይህ የኢየሱስ መስቀል ነው :: መስቀሉን ያልተሸከመ የእርሱ ሊሆን አይችልምና በማለት ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ የስብሰባው ፍጻሜ ሆኖ ተሰነባብተው በእንባ ተለያዩ ::

አለቃ ንዋየክርስቶስ ከደብረታቦር ሰኔ 30 ቀን 1912 ዓ.ም ተነስተው ወደ ነገላ ሄደው ደብረ ሲና ከተባለው አንባ አጠገብ ከሚገኘው ቤታቸው ደረሱ :: ከዚያም እንደደረሱ ለቤተሰቦቻቸው የእረፍት ጊዚያቸው እንደደረሰ ስላስጠነቀቋቸው ባጠገባቸው ልጆቻቼው፡ ወንድሞቻቸውና ተማሪወቻቸው ተሰብስበው ሲጠባበቋቸው ነሀሴ 29 ቀን 1912 ዓ.ም አረፉና ዘመድ ወዳጅ እልቅሶ ሸኛቸው :: ከተማሪወቻቸው መካከል የነበሩት የወለዱኝ አባቴ አለቃ ንጉሤ ቦጋለ እንዲህ ብለው ገጠሙላቸው ::

እንዴት ነው ነገላ የጌቶቹ መንደር፤
የንዋየክርስቶስ የታላቁ መምህር ::
ስለሃይማኖቱ እንደ ኒቆዲሞስ ጠንቅቆ መርማሪ፤
እንደነቢያቶች ትንቢት ተናጋሪ ፤
እንደሐዋርያ ወንጌል አስተማሪ ::
አሁን ምን ይሆናል ይህ ሁሉ ቢወሳ፤
ያለ ሰው ብርቱ ነው የሞተ ኮሣሣ ::
እልፍኝ አዳራሹን ክፈቱት በሩን ፤
ሰው እያየው ይሂድ አለመኖሩን ::

የመጀመርያው ሽህ ዘካርያስ የኋላው አለቃ ንዋየክርስቶስ በተመደበላቸው ቦታ ላይ እርፈው የጌታን ዳግም ምጣት ይጠባበቃሉ ::



<u>ከአታሚው ድርጅት</u>

!!!!! ይህ የአለቃ ነዋየ ክርስቶስን የህይወት ታሪክ ከሞላ ጎደል ሲያስተዋውቀን ብዙወቻችን ተከታዮቻቸው የት ደረሱ ? ብለን ልንጠይቅ እንችላለን ::

ስለተከታዮቻቸው <u>ስደትና ፍትህ</u> በሚል እርእስ የዚህ ሕዝብ ከጎንደር ፤ አርባ ምንጭ፤ ወላይታ ሶዶ፤ ከዛም ጌራ ጅማና ሸዋ ወሊሶ ጉዞ ወደፊት አትመን እንደምናወጣ ልናስታውቃችሁ እንወዳለን ::

ስለዚህ መጽሐፍ አስተያየት ካላችሁም ሆነ ለማዘዝ ከፈለጋችሁ ከዚህ በታች ባለው አድራሻ እንድትጸፉልን በትህትና እንጠይቃለን ::

**The Potter's clay publishing**
P.O. Box 7123
Loma Linda CA, 92354

# ስለደራሲው

ቄስ ብርሃኑ ንጉሤ ጥር 26 ቀን 1912 ተወልደው እድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ አባታቸው የሸህ ዘካርያስ ተማሪ የነበሩ ማንበብና መጻፍ አስተማሯቸው ። በ1926 ዓ/ም በደብረታቦር ከተማ በሸህ ዘካርያስ ተከታዮች ከፍተኛ መስዋእትነት በተሰራው ት/ቤት ትምህርታቸውን ጀመሩ ። ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እንዳሉ አገራችን በጠላት ስለተወረረች ትምህርታቸውን አቋርጠው ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ተገደዱ ። አሁንም ጠላት አካባቢውን ስላቃጠለው ለሁለት አመት ተሰደው የ18 አመት ወጣት በሆኑበት ጊዜ ቤታቸውን ጥለው በመሰደድ በአርበኝነት ጠላት ካገር እስኪወጣ ታግለዋል ። ከዚህም በኋላ ተመልሰው ትምህርታቸውን በመቀጠል የመጀመርያ እርዳታ



ሕክምና ትምህርት ንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ተማሩ ፤ ትምህርታቸውን በመቀጠል በአቃቂ በሰቃና ሻሸመኔ ኩየራ የአስተማሪነትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አጥንተዋል ። በኋላም ወደ ትውልድ አገራቸው በመመለስ በጭልጋ አውራጃና አካባቢው ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችን በመከላከልና በወንጌላውይነት አገለገሉ ። በስራ ታታሪነታቸው አለቆቻቸው 1954 ዓ/ም የድርጅቱ የሰሜን ምዕራብ የስራ መስክ አስተዳዳሪ አድርገው ሾሟቸው። 1959 ዓ/ም ወደ ወላይታ ተዛውረው በወላይታና በአርባ ምንጭ አካባቢ ለሁለት አመት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ገበሬዎችን በማስፈር ትልቅ ቁም ነገር ሰርተዋል ። በድርጅቱ ዋናው መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ የድርጅቱ ነገረ ፈጅና የቤተክርስትያኑ ቄስ በመሆን ከ1961 እስከ 1965 ዓ.ም አገልግለው ወደ ጅማ ተዛወሩ ። እንደገና 1968 ወደ ደብረታቦር ተዛውረው ለአምስት አመት አገለገሉ ። በመጨረሻም ከ1973 ጀምሮ ጡረታ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ በአዲስ አበባ የድርጅቱ የመካከለኛው ስራ መስክ አስተዳዳሪ በመሆን አገልግለዋል ። ቄስ ብርሃኑ ዛሬ ማለትም በ1996 ዓ/ም መጀመርያ ላይ የ84 አመት አዛውንት ናቸው ።